



# የአካባቢ ሳይንስ



## የተማሪ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# የአካባቢ ሳይንስ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል


### አዘጋጆች:-

1. ሙሉቀን ገብሬ(MSc.)
2. እንግዳ ገ/ማርያም(MA)
3. ሁሴን ጀማል(BA)

### አርታኢ:- ሲሳይ አብደላ(MSc.)

### ጥራት አረጋጋጮች

1. ዘላለም ለገሰ(MSc.)
2. ዝናው ዱባለ(MSc.)
3. መሃመድናጂ እስማኤል(MA)

### ሌያውት ዲዛይን:- ኃይለማርያም መለሰ (MSc.)



የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ትምህርት ቢሮ

## © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው።

# ማውጫ


መግቢያ ....................................................i

## ምዕራፍ አንድ 1

### የክልላችን መገኛ ................................ 1

1.1. የአካባቢያችን መገኛ ........................................................ 2
1.2. አራቱ አቅጣጫዎች ........................................................ 5
1.3. የቤት፣ የትምህርት ቤትና የቀበሌ መገኛ ................................ 8
1.4. የጎረቤቶቻችን መገኛና አቅጣጫ ........................................ 12

## ምዕራፍ ሁለት 16

### ሳይንስን ማስተዋወቅ ................................ 16

2.1. የሰውነት ክፍሎች ........................................................ 17
2.2. የግል ንጽህና አጠባበቅን መለማመድ ................................ 21
2.3. አምስቱ የስሜት ህዋሳት ትስስር ....................................25
2.4. ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ ........................................ 31
2.5. በአካባቢ ዉስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ........................................ 32
2.6. ብርሃን ምንድነዉ? ........................................................ 37

## ምዕራፍ ሶስት 42

### የተፈጥሮ አካባቢ ............................... 42

3.1. የአካባቢያችን አየር ሁኔታ ............................................ 43

3.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች .................... 46

3.3. ንፅህናና የግል ንፅህና ................................................ 60

## ምዕራፍ አራት 68

### ማህበራዊ አካባቢ ............................... 68

4.1. የቤተሰብ አባላትና ሚናዎቻቸው.......................................... 69

4.2. ለመኖር ምን ያስፈልጋል? ............................................ 74

4.3. በትምህርት ቤታችን ውስጥ ምን እናገኛለን? ...................... 77

4.4. በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንስራ ....................................... 80

4.5. የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎች .................................. 83

## ምዕራፍ አምስት 88

### የተለየ ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ ጉዳዮች ....... 88

5.1. የመንገድ አጠቃቀም ................................................. 89

5.2. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ........................................ 93

### ዋቢ መጽሐፍት ....................................... 99

# መግቢያ

ይህ የ1ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በአማርኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነዉ። መጽሐፉ የአካባቢ ሳይንስ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች የአካባቢያቸዉን የተፈጥሮአዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ ኩነቶችን እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል። መጽሐፉ ተማሪዎች የፈጠራ ክህሎታቸውን በእጅጉ ለማሳደግ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች ለሚቀጥለዉ የክፍል ደረጃ አስፈላጊዉን ብቃት ይዘዉ ለመሻገር ይጠቅማቸዋል። ስለሆነም መጽሐፉ የሚከተሉትን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል።

1. ተማሪዎች ስለአካባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ያላቸዉን
2. ግንዛቤ ለማዳበር
3. ተማሪዎች ስለሰዉነት ክፍሎች እና ስለጥንቃቄዎች በቂ እዉቀት እንዲኖራቸዉ ለማስቻል
4. ተማሪዎች አካባቢያቸዉን በማወቅ የአካባቢያቸዉን
5. የተፈጥሮ ሁኔታዎችን እንዲረዱና እንዲጠብቁ ለማስቻል
6. ተማሪዎች ማህበራዊ ጉዳዮችና ግንኙነቶች አስፈላጊዉን እዉቀት እንዲጨብጡ ለማድረግ
7. ተማሪዎች ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ጉዳዮችን (cross cutting issues) ተገንዝበዉ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማነሳሳት ዋነኛ አጋዥ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ ተዘጋጅቷል።

ስለሆነም መጽሐፉ በቅደም ተከተል የአካባቢያችን መገኛ፣ የሰዉነት ክፍሎች፣ የተፈጥሮ አካባቢ፣ ማህበራዊ አካባቢ እና ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ጉዳዮች የሚሉ አምስት ምዕራፎችን ይዟል። እነዚህ ምዕራፎች የተማሪዎችን አጥጋቢ መሰረታዊ ዕዉቀት የሚጠይቁ እና ለቀጣይም የበለጠ እንዲያሳድጉ ታስቦ ተዘጋጅቷል።

እያንዳንዱ ምዕራፍ በተለያዩ ይዘቶች የተከፋፈለ ነዉ። እነዚህ ይዘቶች ደግሞ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ የተማሪ ተግባራት፣ መልመጃዎች፣ የምዕራፉ ማጠቃለያ እና የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎችን ያጠቃልላሉ።

# ምዕራፍ አንድ

# የክልላችን መገኛ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የቦታን ፅንሰ-ሀሳብ ታብራራላችሁ፡፡
- የግራ፣ የቀኝ፣ የፊት እና የኋላ አቅጣጫዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ከሌሎች ቦታዎች አንፃር የአካባቢ መገኛ እንዴት እንደሚገለፅ ታብራራላችሁ፡፡
- የግራ፣ የቀኝ፣ የፊት እና የኋላ አቅጣጫዎችን በመጠቀም በዙሪያችሁ ያሉትን ነገሮች ትለያላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የአንዱን ገጽታ አቅጣጫ ከሌላው አንፃር ትገልፃላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁን እንዲሁም የቤታችሁን እና የጎረቤታችሁን መገኛ ታመለክታላችሁ፡፡
- ቀለል ያለ የአካባቢ ካርታ ትስሉና የትምህርት ቤታችሁን አንፃራዊ መገኛ ታሳያላችሁ፡፡

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

**1.1.** የአካባቢያችን መገኛ

**1.2.** አራቱ አቅጣጫዎች

**1.3.** የቤት፣ የትምህርት ቤት እና የቀበሌ መገኛ

**1.4.** የጎረቤቶቻችን መገኛና አቅጣጫ

## መግቢያ

ዉድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአካባቢ መገኛ በሚለው ዋና ርዕስ ስር አቅጣጫን በመናገር፣ አራቱን አቅጣጫዎች በማሳየት፣ የቤት፣ የትምህርት ቤት እና የቀበሌ መገኛ እንዲሁም የጎረቤት መገኛና አቅጣጫ መለየትና ማሳየት ነው፡፡

# 1.1. የአካባቢያችን መገኛ



### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- አቅጣጫ
- ጠቋሚ
- መኖሪያ
- አካባቢ
- መገኛ
- ጤና ጣቢያ

## የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ቤታችሁ የሚገኝበትን አቅጣጫ ትናገራላችሁ፡፡
- የአካባቢያችሁን አቅጣጫ ትጠቁማላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

1.1.1 አቅጣጫን መናገር


1.1.2 የአቅጣጫ ጥቅም

## 1.1.1. አቅጣጫን መናገር

### ተግባር 1.1.1 የማስተዋል ጥያቄ

ዓላማ:- የመኖሪያ ቤት አቅጣጫን ማሳየት

ጥያቄ:- ቤታችሁ የሚገኝበትን አቅጣጫ ተናገሩ፡፡



ስዕል 1.1 የቤት አቅጣጫ ማሳየት

ከስዕሉ ላይ ምን ተመለከታችሁ?

ከላይ በስዕሉ ላይ ለማየት እንደቻላችሁት የተማሪው ወይም የተማሪዋ ቤት ከትምህርት ቤቱ በስተቀኝ፣ ከጤና ጣቢያ በስተግራ ይገኛል፡፡ ስለዚህ እናንተም የምትገኙበትን ቦታ ለመግለፅ አቅጣጫ ያስፈልጋል፡፡

አቅጣጫ ማለት የአንድን ነገር መገኛ ቦታን የሚገልፅ ማሳያ ወይም ጠቋሚ ነው፡፡

## 1.1.2. የአቅጣጫ ጥቅም

### ተግባር 1.1.2 የቡድን ውይይት

ዓላማ:- የአቅጣጫን ጥቅም መግለፅ


**መመሪያ፡-** በቡድን በመሆን ስለ አቅጣጫ ጥቅም ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ

**ጥያቄ፡-** አቅጣጫ ለምን ይጠቅማል?

አቅጣጫ የመኖሪያ አካባቢን ለመለየትና ለማሳየት ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ቤታችሁን መገኛ ቦታ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

## መልመጃ 1.1

**ትዕዛዝ 1:** ስዕሉን በማየት ትምህርት ቤቱ የሚገኝበትን አቅጣጫ የሚያመለክተውን ቁጥር በባዶ ቦታዎች ላይ ፃፍ/ፊ፡፡




**ምሳሌ፡-** ቁጥር 4 መንገዱ ከመኖሪያ ቤት ፊት ለፊት መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሀ. ቁጥር __________ ከመኖሪያ ቤት በስተጀርባ ይገኛል፡፡

ለ. ቁጥር __________ ከመኖሪያ ቤት በስተቀኝ ይገኛል፡፡

ሐ. ቁጥር __________ ከመኖሪያ ቤት በስተግራ ይገኛል፡፡

**ትዕዛዝ 2፡-** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡

1. አቅጣጫን ለመለየት __________ ይጠቅማል፡፡

   ሀ. አካባቢ ሐ. መኖሪያ ቤት

   ለ. ትምህርት ቤት መ. ሁሉም

2. __________ የአንድ ነገር መገኛ ቦታን የሚገልፅ ማሳያ ነዉ፡፡

   ሀ. አቅጣጫ ሐ. ሰዉ

   ለ. ቤት መ. ሁሉም

## 1.2. አራቱ አቅጣጫዎች



**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ፀሐይ
- ምዕራብ
- ምስራቅ
- ሰሜን
- ደቡብ
- ኮምፓስ

### የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- አራቱን አቅጣጫዎች ትዘረዝራላችሁ::
- አራቱን አቅጣጫዎች በመጠቀም የአካባቢያችሁን አንፃራዊ መገኛ ትለያላችሁ::
- አራቱን አቅጣጫዎች በመጠቀም አካባቢያችሁን ትናገራላችሁ::

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

1.2.1 የአራቱ አቅጣጫዎች ዝርዝር

1.2.2 ኮምፓስ በመጠቀም አቅጣጫን መለየት

### 1.2.1. የአራቱ አቅጣጫዎች ዝርዝር

**ተግባር 1.2.1 የቡድን ዉይይት**


**ዓላማ:-** አቅጣጫዎችን መዘርዘር

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

**ጥያቄ:-** 1. የፀሐይ መውጫ አቅጣጫን አሳዩ::

2. የፀሐይ መግቢያ አቅጣጫን አሳዩ::

3. አራቱን አቅጣጫዎች ዘርዝሩ::



ስዕል 1.2 አቅጣጫን ማሳየት

በሥዕል 1.2 እንደሚታየው ፊታችሁን ወደ ፀሐይ መውጫ መልሱና እጃችሁን ወደ ግራና ወደ ቀኝ ዘርግታችሁ ቁሙ:: ከአቋቋማችሁ አኳያም ከፊት ለፊታችሁ ያለው አቅጣጫ ወይም የፀሐይ መውጫ ምስራቅ ይባላል:: በጀርባችሁ በኩል ያለው ደግሞ ፀሐይ የምትጠልቅበት ምዕራብ ይባላል:: እንዲሁም የግራ እጃችሁ አቅጣጫ ሰሜን ሲሆን፤ የቀኝ እጃችሁ አቅጣጫ ደግሞ ደቡብ ይባላል::


## 1.2.2. ኮምፓስ በመጠቀም አቅጣጫን መለየት

### ተግባር 1.2.2 የጥንድ ወይይት

**ዓላማ:-** የኮምፓስን ጥቅም እና አሰራሩን ማብራራት

**መመሪያ:-** በጥንድ በመወያየት የኮምፓስን ጥቅም እና አሰራሩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

**ጥያቄ:-** ኮምፓስ ምንድነዉ? ለምንስ ያገለግላል?




ስዕል 1.3 ኮምፓስ

ኮምፓስ አቅጣጫን ለማመልከት የሚያገለግል መሳሪያ ነዉ።

ኮምፓስ በአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች ሊሰራ የሚችል መሳሪያ ነዉ።

## ተግባራዊ ክንዋኔ 1.1 የኮምፓስ አሰራር

ኮምፓስ ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮች:

ካርቶን ወይም ኮምፐርሳቶ፣ እርሳስ፣ መቀስ፣ ሚስማር ወይምስፒልና እንጨት

## የአሰራር ቅደም ተከተል

1. ካርቶኑን በክብ ቅርፅ መቁረጥና በእኩሌታ ላይ መብሳት

1. ሌላ ተጨማሪ ካርቶን ወይም ኮምፐርሳቶን በሶስት ማዕዘን ወይም በቀስት ቅርፅ መቁረጥ

1. በተዘጋጀው እንጨት ላይ በአግድም ቀስቱን በሚስማር ማያያዝ

1. እርሳሱን ከተዘጋጀው ቀስት ጋር በስፒል ማያያዝ

ውጤት: ኮምፓሱ ከተሰራ በኋላ ቀስቱን በማሽከርከር አራቱን አቅጣጫዎች ማሳየት

መልመጃ 1.2

**ትዕዛዝ 1:-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት"ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ::

1. ኮምፓስ አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ነዉ::
2. የፀሐይ መግቢያ አቅጣጫ ሰሜን ይባላል::

**ትዕዛዝ 2:-** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ::

1. ፊታችሁን ወደ ፀሐይ መግቢያ መልሳችሁ ብትቆሙ በጀርባችሁ ያለው አቅጣጫ ምን ይባላል?
   - ሀ. ደቡብ
   - ሐ. ምስራቅ
   - ለ. ሰሜን
   - መ. ሁሉም
2. ፊታችንን ወደ ፀሐይ መውጫ ብናደርግ የቀኝ እጃችን የትኛውን አቅጣጫ ያመለክታል?
   - ሀ. ሰሜን
   - ሐ. ምስራቅ
   - ለ. ደቡብ
   - መ. መልስ የለም

## 1.3. የቤት፣ የትምህርት ቤትና የቀበሌ መገኛ



**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- መንደር
- ቀበሌ
- ቤት
- ትምህርት ቤት

መገኛ ማለት አንድ ነገር ያረፈበት ቦታ ማለት ነው::

**የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የቤታችሁን መገኛ ትናገራላችሁ
- የትምህርት ቤታችሁን መገኛ ትናገራላችሁ

- የቀበሌያችሁን መገኛ ትለያላችሁ

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

1.3.1 የቤታችን መገኛ

1.3.2 የትምህርት ቤታችን መገኛ

1.3.3 የቀበሌያችን መገኛ

## 1.3.1. የቤታችን መገኛ

### ተግባር 1.3.1 የማስተዋል ጥያቄ

**ዓላማ:-** የቤት አቅጣጫ መናገር

**ጥያቄ:-** የፀሐይን መውጫ አቅጣጫ በመጠቀም የመኖሪያ ቤታችሁ የት አካባቢ እንደሚገኝ ተናገሩ::




ስዕል 1.4 የቤት አቅጣጫ ማሳየት

ከላይ በስዕል 1.4 እንደተመለከተው የመኖሪያ ቤት የሚገኘው ከቀበሌዉ ፊት ለፊት ነው:: የመኖሪያ ቤት መገኛ ለማወቅ አራቱን አቅጣጫዎች መለየት አስፈላጊ ነው::

የመኖሪያ ቤት:- አንድ ቤተሰብ አንድ ላይ አብሮ የሚኖርበት መጠለያ ቦታ ነው::

የቤታችን መገኛ:- ቤታችን ከሌላ ቦታ አንፃር ያረፈበት ወይም የሰፈረበት ቦታ ማለት ነው::

## 1.3.2. የትምህርት ቤታችን መገኛ

### ተግባር 1.3.2 የቡድን ውይይት

ዓላማ:- ስለ ትምህርት ቤት ማብራራት

መመሪያ:- የተወያያችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ::

ጥያቄ:- 1. በትምህርት ቤታችሁ ዉስጥ ምን ይገኛል?

2. የትምህርት ቤታችሁን አቀጣጫ ስዕል በመሳል አሳዩ::



ስዕል 1.5 ትምህርት ቤት

ከላይ በስዕል 1.5 እንደ ተመለከታችሁት በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያሉ ነገሮች

- ሰንደቅ ዓላማ
- አትክልቶች
- ዛፎች
- የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ እና
- ተማሪዎች ይገኛሉ::

ውድ ልጆች! በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮች አንፃራዊ መገኛ አብራሩ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ሰንደቅ ዓላማ ከመማሪያ ክፍሎች ፊት ለፊት ይገኛል እንዲሁም ዛፎች ከሰንደቅ ዓላማ በስተጀርባ ይገኛሉ፡፡ ትምህርት ቤታችሁ ከቤታችሁ ወዴት እንደሚገኝ ለማወቅ አራቱን አቅጣጫዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም አቅጣጫዎች ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ ናቸው፡፡ ከዚህም በመነሳት የትምህርት ቤታችሁ አቅጣጫ ከቤታችሁ በየትኛው በኩል እንደሚገኝ መለየት ትችላላችሁ፡፡

## 1.3.3. የቀበሌያችን መገኛ

ቀበሌ ማለት የአካባቢ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ቦታ ነዉ፡፡ ነው፡፡

### ተግባር 1.3.3 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** ስለ ቀበሌያችሁ መገኛ ማብራራት

**መመሪያ፡-** የተወያያችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ

**ጥያቄ፡-** 1. ቀበሌ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
የቀበሌያችሁ ስም ማን ይባላል?
2. የቀበሌያችሁን አቅጣጫ የንድፍ ካርታ በመሳል አሳዩ፡፡




ስዕል 1.6 የቀበሌ መገኛ

በሥዕል 1.6 ላይ ምን ተመለከታችሁ? በእናንተ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙት የትኞቹ ናቸው?

ከላይ በስዕል 1.6 እንደተመለከተዉ የነአሰገደች መኖሪያ ቤት ከቀበሌዉ ፊት ለፊት ይገኛል፡፡ አሰገደች ሁል ጊዜ ጠዋት ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት በቀበሌው ፊት ለፊት ባለው ትልቁ መንገድ ትሄዳለች፡፡ የነአሰገደች ትምህርት ቤት የሚገኘው ከቀበሌዉ በስተግራ በኩል ነው፡፡ ከቀበሌው በስተጀርባ ጥቅጥቅ ያለ ደን ይገኛል፡፡

### መልመጃ 1.3

**ትዕዛዝ 1:-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. አቅጣጫን በመጠቀም የቤታችንን መገኛ እናሳያለን፡፡
2. ትምህርት ቤት ዉስጥ ቤተ-መፃህፍት ይገኛል፡፡

**ትዕዛዝ 2:-** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡

1. ከሚከተሉት የትኛዉ በትምህርት ቤታችን ዉስጥ ይገኛል
   ሀ. ሰንደቅ ዓላማ ሐ. መፀዳጃ ቤት
   ለ. መማሪያ ክፍል መ. ሁሉም
2. ከሚከተሉት አንዱ ተማሪዎች ተሰባስበዉ የሚማሩበት ቦታ ነዉ፡፡
   ሀ. ቀበሌ ሐ. ገበያ
   ለ. ትምህርት ቤት መ. ቤት

## 1.4. የጎረቤቶቻችን መገኛና አቅጣጫ



### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ጎረቤት
- ሠላም
- ቤተሰብ
- ደስታ
- መረዳዳት
- መቀራረብ

## የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች! ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የጎረቤታችሁን መገኛ አቅጣጫ ትናገራላችሁ::
- የጎረቤታችሁን መገኛ ቀለል ያለ ስዕል በመሳል ታሳያላችሁ::

### 1.4.1. የጎረቤታችን መገኛ

**ተግባር 1.4.1 የቡድን ውይይት**


ዓላማ:- የጎረቤት መገኛን በስዕል ማሳየት

መመሪያ:- በቡድን ሆናችሁ የአንዱን ተማሪ ቤት መርጣችሁ የጉረቤት መገኛ በንድፍ ካርታ ሳሉና ለመምህራችሁ አሳዩ::

ጥያቄ:- 1. የጎረቤታችሁን ቤት መገኛ በንድፍ ካርታ አሳዩ::

2. የመረጣችሁትን ተማሪ ጎረቤት ቤት አቅጣጫ መገኛ አሳዩ::

ጎረቤት:- በአንድ አካባቢ ተቀራርበው የሚኖሩ ሰዎች ሲሆኑ በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜ ይረዳዳሉ::




ስዕል 1.7 የጎረቤታሞች መገኛ

ከላይ በስዕል 1.7 እንደተመለከተው የጎረቤት ቤት ከመንገድ ጀርባ ከሱቁ በስተግራና ከነጌታቸው ቤት በስተቀኝ በኩል ይገኛል::

## መልመጃ 1.4

**ትዕዛዝ 1:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ።**

1. የጎረቤታችን ቤት ለመለየት ምን እንጠቀማለን?

ሀ. አቅጣጫ    ሐ. ካርታ

ለ. ኮምፓስ    መ.ሁሉም

2. ጎረቤታሞች__________ይኖራሉ።

ሀ. በመደጋገፍ    ሐ. በመተባበር

ለ. በመረዳዳት    መ. ሁሉም

**ትዕዛዝ 2: የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።**

1. ጎረቤት ማለት ምን ማለት ነው?

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

አቅጣጫ የአንድን ነገር መገኛ ቦታን የሚገልፅ ማሳያ ወይም ጠቋሚ ነው።

የአካባቢዎች መገኛ በአራቱ አቅጣጫዎች ይገለፃል። እነዚህም ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ናቸዉ።

አቅጣጫ መኖሪያ አካባቢ ለመለየት እና የትምህርት ቤት መገኛ ቦታ ለማወቅ ይጠቅማል።

**መገኛ:-** አንድ ነገር ያረፈበት ቦታ ማለት ነው።

**ቤት:-** አንድ ቤተሰብ አንድ ላይ አብሮ የሚኖርበት መጠለያ ቦታ ነው።

የቤታችን መገኛ:- ቤታችን ከሌላ ቦታ አንፃር ያረፈበት ቦታ ነው።

**ቀበሌ:-** የአካባቢ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ቦታ ነው።

**ጎረቤት:-** በአንድ አካባቢ ተቀራርበው የሚኖሩ ሰዎች ማለት ሲሆን ጎረቤታሞች በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜ ይረዳዳሉ።

## የምዕራፍ አንድ የክለሳ መልመጃዎች

**ትዕዛዝ 1፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. አቅጣጫ የትምህርት ቤታችንን መገኛ ያሳያል፡፡
2. የፀሐይ መውጫ የምስራቅ አቅጣጫን ያመለክታል፡፡
3. አንድ ቤተሰብ የሚኖርበት መጠለያ ቤት ይባላል፡፡

**ትዕዛዝ 2፡ አቅጣጫዎችን ከትክክለኛ መግለጫ ጋር በመስመር/ በቀስት አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ኮምፓስ | ሀ. የፀሐይ መግቢያ |
| 2. ምስራቅ | ለ. አቅጣጫ ጠቋሚ |
| 3. ምዕራብ | ሐ. የፀሐይ መውጫ |

**ትዕዛዝ 3፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ______ የአንድን ነገር መገኛ ቦታ የሚጠቁም ነው፡፡
   ሀ. ቤተሰብ ለ. አቅጣጫ ሐ. ሰዎች መ. ሁሉም
2. አንድ ነገር ያረፈበት ቦታ ምን ይባላል
   ሀ. መገኛ ለ. አቅጣጫ ሐ. ቤተሰብ መ. ሰዉ
3. በአንድ አካባቢ ተቀራርበው የሚኖሩ ሰዎች ወይም ቤተሰቦች ምን ይባላሉ?
   ሀ. አቅጣጫ ለ. መገኛ ሐ. ጎረቤት መ. ሱቅ
4. ሰዎች ለስብሰባ የሚገኙበት ቦታ ምን ይባላል?
   ሀ. መገኛ ለ. ቀበሌ ሐ. አቅጣጫ መ. መኖሪያ
5. ከሚከተሉት ውስጥ አቅጣጫን የማይገልፅ የቱ ነው
   ሀ. ሰሜን
   ለ. ምስራቅ
   ሐ. ቤተሰብ
   መ. ደቡብ

# ምዕራፍ ሁለት

# ሳይንስን ማስተዋወቅ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ስም ትናገራላችሁ::
- የአምስቱን የስሜት ህዋሳት ጥቅሞች ታብራራላችሁ::
- የስሜት ህዋሳትን ትስስር ትለያላችሁ::
- በቤትና በትምህርት ቤት አካባቢ ያሉ ቁሳቁሶችን ትዘረዝራላችሁ::
- የግል ንጽህና አጠባበቅን ትመለከታላችሁ፤ ትለማመዳላችሁ::
- ጨለማ የብርሃን ያለመኖር መሆኑን ትገነዘባላችሁ::

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

2.1. የሰውነት ክፍሎች

2.2. የግል ንጽህና አጠባበቅን መለማመድ

2.3. አምስቱ የስሜት ህዋሳት ትስስር

2.4. ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ

2.5. በአካባቢ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶች

2.6 ብርሃን ምንድነዉ?

## መግቢያ

ዉድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የሰዉነት ክፍሎች ትርጉም፣ ዉጫዊ የሰውነት ክፍሎች ዝርዝር፣ ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ ማድረግ፣ የግል ንፅህና አጠባበቅን መለማመድ፣ የአምስቱ የስሜት ህዋሳት ትስስር፣ ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መውሰድ፣ እንዲሁም በአካባቢ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶች እና ስለ ብርሃን ምንነት ትማራላችሁ።

## 2.1. የሰውነት ክፍሎች



### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- የሰዉነት ክፍል
- ጭንቅላት
- ፊት

### ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ስም ትናገራላችሁ።
- ዋና ዋና ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ታሳያላችሁ።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ጥንቃቄ ትለማመዳላችሁ።

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

2.1.1 የሰውነት ክፍሎች ትርጉም
2.1.2 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች
2.1.3 የውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ


### 2.1.1. የሰውነት ክፍሎች ትርጉም

**ተግባር 2.1.2 የቡድን ውይይት**

**ዓላማ:-** የሰውነት ክፍሎችን መግለፅ

**መመሪያ:-** ስለ ሰዉነት ክፍሎች በቡድን የተወያያችሁትን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ:-** የሰዉነት ክፍሎች ማለት ምን ማለት ነዉ?




ስዕል 2.1 ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎች

የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት ራስ ወይም ጭንቅላት፣ ሆድ፣ እጅና እግር የመሳሰሉት በአንድ ላይ በመሆን ሰው የተሟላ የሰዉነት ክፍል እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህ የሰውነት ክፍሎች የተለያየ አገልግሎት ይሰጣሉ።

## 2.1.2. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች


### ተግባር 2.1.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** ውጫዊ የሰዉነት ክፍሎችን መዘርዘር

**መመሪያ:-** በጥንድ እየሆናችሁ በመወያየት ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ:-** 1. ውጫዊ የሰዉነት ክፍሎች የትኞቹ ናቸዉ?

2. ተማሪዎች! ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎችን አሳዩ።




ስዕል 2.2 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

ውጫዊ የሰዉነት ክፍሎች፡- ፀጉር፣ ዓይን፣ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ግንባር፣ አንገት፣ ትከሻ፣ ደረት፣ እጅ እና እግር የመሳሰሉት ናቸዉ።

## 2.1.3. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችና ጥንቃቄ

### ተግባር 2.1.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ ማብራራት

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት ያገኛችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ፡-** ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን እንዴት ከአደጋ መጠበቅ ይቻላል? አደጋዎችስ ምን ምን ናቸዉ?



ስዕል 2.3 ልጁ ምን እያደረገ ነዉ

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ ካልተደረገ ለተለያዩ አደጋዎችና በሽታዎች ይጋለጣሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-**

1. የተለያዩ ስለታማ ነገሮችን ያለአግባብ መጠቀም ውጫዊ አካል ክፍሎችን ይጎዳል፡፡
2. ልጆች ፊታቸዉንና ገላቸዉን በትክክል ካልታጠቡ ለተለያዩ በሽታዎች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

## መልመጃ 2.1

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. ገላችንን በየጊዜዉ ካልታጠብን ለበሽታ ያጋልጠናል፡፡
2. የፀጉርን ንፅሕና መጠበቅ ውበትን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡

**ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ከአንገት በላይ የሆነዉ የአካል ክፍል የትኛዉ ነዉ?

   ሀ. ሆድ ለ. ጆሮ ሐ. እግር መ. ሁሉም

2. ______ጭንቅላታችንን ከብርድ ይከላከላል፡፡

   ሀ. ፀጉር ለ. ሆድ ሐ. ደረት መ. አፍንጫ

## 2.2. የግል ንጽህና አጠባበቅን መለማመድ



### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ንፅህና
- በሽታ
- መታጠብ
- መጉመጥመጥ
- ብሩሽ

### የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- የግል ንጽህና አጠባበቅን ከስዕሎች በማየት ታስተዉላላችሁ፡፡
- የግል ንጽህና አጠባበቅን ትለማመዳላችሁ፡፡

### 2.2.1. የግል ንጽህና አጠባበቅን መለማመድ

**ተግባር 2.2.1 የጥንድ ዉይይት**

**ዓላማ:-** የግል ንፅህና አጠባበቅን ማብራራት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት ያገኛችሁትን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

**ጥያቄ:-** 1. የግል ንፅሕና መጠበቅ ለምን ያስፈልጋል?

2. የሰዉነት ክፍሎቻችሁን ንፅሕና ለመጠበቅ ምን ትጠቀማላችሁ?

የሰዉነት ክፍሎቻችን የተሟላ ሥራ እንዲሰሩ ንፅሕናቸው በሚገባ መጠበቅ አለበት፡፡

የግል ንፅሕና ካልጠበቅን በተለያዩ በሽታዎች ልንጠቃ እንችላለን፡፡

በአካባቢያችሁ የግል ንፅሕና ባለመጠበቅ የሚመጡ በሽታዎች ምንድናቸው? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡






ስዕል 2.4 ልጆች የግል ንፅህናቸዉን ሲጠብቁ

ጠዋት ጠዋት ከመኝታችን እንደተነሳን እጃችንንና ፊታችንን በሳሙናና በንፁህ ውሃ መታጠብ አለብን፡፡

ምግብ ከመመገባችን በፊት ዘወትር በሳሙናና በንፁህ ውሃ መታጠብ ተገቢ ነዉ፡፡



ስዕል 2.5 የጥርስ ንፅህና መጠበቅ

ዘወትር ጠዋት ጠዋት የጥርሳችንን ንፅህና መጠበቅ አለብን፡፡

ምግብ ከተመገብን በኋላ አፋችንን በንፁህ ውሃ መጉመጥመጥ አለብን፡፡ በጥርሶቻችን መካከል የቀረውን ምግብ በባህላዊ ወይም በዘመናዊ መፋቂያ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡





ስዕል 2.6 የፀጉር ንፅህና መጠበቅ

የፀጉርን ንፅሕና መጠበቅ ጤንነታችንንና ውበታችንን ለመጠበቅ ይረዳናል፡
፡

ቅማል፣ ቅጫምና የመሳሰሉት ጥገኛ ሕዋሳት ምን ዓይነት ጉዳቶችን ያስከትላሉ?

- በሽታን ከሰው ወደ ሰው ያስተላልፋሉ፡፡
- በቆዳችን ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡



ስዕል 2.7 ልጁ ምን እያደረገ ነዉ?

በአፍንጫ ቀዳዳ አቧራ ገብቶ በሽታ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህ

አፍንጫችንን በንፁህ መሀረብ ወይም ጨርቅ ማፅዳት ያስፈልጋል፡፡

### የገላ ንፅህና አጠባበቅ





ስዕል 2.8 ሰዎች ምን እየሰሩ ነዉ?

## ገላችንን በየጊዜው ካልታጠብን፡-

- ለበሽታ ያጋልጠናል እንዲሁም መጥፎ ጠረን ይኖረናል፡፡
- ውበታችንን ይቀንሳል፡፡

ስለዚህ ልጆች! በየጊዜው የሰውነታችንን ንፅሕና መጠበቅ አለብን፡፡

### የእግር ንፅህና አጠባበቅ



ስዕል 2.9 የእግር ንፅህና መጠበቅ

እግራችንን በየቀኑ መታጠብና ንፅሕናውን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እግራችንን ያለመታጠብ መጥፎ ሽታ ያስከትላል፡፡ በተጨማሪ የእግራችንን ጤንነት ለመጠበቅ ጫማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ጫማ የማድረግ ጥቅም ፡-**

- የመሬት ትላትሎች እንዳይጎዱን ይረዳናል፡፡
- የዛጉና ስለት ያላቸው ነገሮች እንዲሁም እሾህ እንዳይወጋን ይከላከልልናል፡፡
- ድንጋይ ወይም እንቅፋት እንዳይመታን ይከላከልልናል፡፡

### መልመጃ 2.2

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. የግል ንፅህናን መጠበቅ ለጤንነት ይጠቅማል፡፡
2. ምግብ ከተመገብን በኋላ አፋችንን በንፁህ ውሃ መጉመጥመጥ አለብን፡፡

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ጠዋት ከመኝታችን ስንነሳ እጃችንንና ፊታችንን በ___መታጠብ አለብን፡፡
   ሀ. ዉሃ ለ. ሳሙና ሐ. በሁለቱም
2. የግል ንፅህና የሚባሉት
   ሀ. እግር መታጠብ ሐ. ገላ መታጠብ
   ለ. ፊት መታጠብ መ. ሁሉም

## 2.3. አምስቱ የስሜት ህዋሳት ትስስር



**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ህዋሳት
- ሽታ
- ጣዕም
- መዳሰስ

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

2.3.1 አምስቱ የስሜት ህዋሳት ምንነት
2.3.2 አምስቱ የስሜት ህዋሳት ተግባራት

## የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- አምስቱን የስሜት ህዋሳት ትዘረዝራላችሁ::
- የስሜት ህዋሳትን ትስስር ትለያላችሁ::
- አምስቱን የስሜት ህዋሳት በተግባር ታሳያላችሁ::


## 2.3.1. የአምስቱ ስሜት ህዋሳት ምንነት

### ተግባር 2.3.1 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** አምስቱን የስሜት ህዋሳት ማብራራት

**መመሪያ:-** በቡድን ሆናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::

**ጥያቄ:-** አምስቱ የስሜት ህዋሳት እነማን ናቸው?




ስዕል 2.10 አምስቱ የስሜት ህዋሳት

### አምስቱ የስሜት ህዋሳት የሚባሉት:-

- ዓይን፣ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ምላስ እና እጅ ናቸዉ::

## 2.3.2. የአምስቱ ስሜት ህዋሳት ተግባራት

### ተግባር 2.3.1 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** አምስቱን የስሜት ህዋሳት ማብራራት

**መመሪያ:-** በቡድን ሆናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::

**ጥያቄ:-** 1. የአምስቱን ስሜት ህዋሳት ተግባራት አብራሩ::

### 1. ምላስ



ስዕል 2.11 ልጆቹ የተለያዩ ጣዕም ሲቀምሱ

ልጆች! ሁሉም የምግብ አይነቶች አንድ አይነት ጣዕም አላቸው? ሁሉንም ነገር መቅመስ ጥሩ ነው?

ምላስ ለመቅመስ ይጠቅማል:: በመቅመስ የተለያዩ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች መለየት እንችላለን:: ለምሳሌ:- ሙዝ ጣፋጭ ነዉ፤ ግራዋ መራራ ነዉ፤ ሎሚ ኮምጣጣ ነዉ::

ሁሉንም ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር መቅመስ ተገቢ አይደለም::

## 2. አይን




ስዕል 2.12 ልጁ አበባን በትኩረት ሲመለከት

አይን በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን ለማየት ይጠቅማል፡፡ አይናችንን ተጠቅመን አካባቢያችንን ለማየት የብርሃን ምንጭ ያስፈልገናል፡፡

## 3. ጆሮ

ልጆች! ጆሮ ለምን እንደሚጠቅም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

በአካባቢያችሁ ያሉ የእንስሳት ድምፆችን በማስመሰል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሰሙ፡፡



ስዕል 2.13 ልጁ ምን እያደረገ ነዉ?

ጆሮ ድምፅን ለመስማት የምንጠቀምበት የስሜት ሕዋስ ነው፡፡

በተጨማሪ የምንሰማው ድምፅ ከየትኛው አቅጣጫ እንደመጣና የምን ድምፅ እንደሆነ ለመለየት ይረዳናል፡፡


ለምሳሌ:- ው…ው…ው… የውሻ ድምፅ

በኣ..በኣ.. የበግ ድምፅ

## 4. አፍንጫ

ውድ ልጆች! 1. አፍንጫ ለምን ይጠቅማል?

ሁሉም ነገሮች አንድ አይነት ሽታ አላቸው?




ስዕል 2.14 ልጆቹ ምን እያደረጉ ነዉ?

አፍንጫ ለማሽተት ይጠቅማል፡፡ በማሽተት የተለያዩ ሽታ ያላቸዉን ነገሮች መለየት ይቻላል፡፡



ስዕል 2.15 የተለያዩ ሽታ ያላቸዉ ነገሮች

የተለያዩ ነገሮች የተለያየ ሽታ አላቸዉ፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ሽታ ያላቸዉን ነገሮች ማሽተት ለጤና ጠንቅ ነው፡፡

## 5. እጅ



ስዕል 2.16 ልጅቷ ድመት እየዳሰሰች

እጅ የተለያዩ ነገሮችን ለመዳሰስ ይጠቅማል፡፡ በእጅ በመዳሰስ ለስላሳና ሻካራ ነገሮችን መለየት ይቻላል፡፡

### መልመጃ 2.3

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. የስሜት ህዋሳት የሚባሉት አራት ናቸዉ፡፡
2. ጆሮ ከስሜት ህዋሳት አንዱ ነዉ፡፡

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ የስሜት ህዋስ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. አይን
   - ለ. አፍንጫ
   - ሐ. ጆሮ
   - መ. እግር
2. ከሚከተሉት ዉስጥ የአይን ጥቅም የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ለማየት
   - ለ. ለማሽተት
   - ሐ. ለመቅመስ
   - መ. ሁሉም

## 2.4. ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ

**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ንፅህና
- በሽታ
- መታጠብ
- መጉመጥመጥ
- ብሩሽ

### የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ለሌሎች ጤና ሀላፊነት ትወስዳላችሁ፡፡
- ለሌሎች ጤና ሀላፊነት የመዉሰድ ልምድ ታዳብራላችሁ፡፡

### 2.4.1. ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ

**ተግባር 2.4.1 የቡድን ውይይት**

**ዓላማ:-** ለሌሎች ጤና ሀላፊነት ስለመዉሰድ ማብራራት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት የተስማማችሁበትን የዉይይት ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

**ጥያቄ:-** ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ እንዴት ይቻላል?



ስዕል 2.17 ስለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ

ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ የሚቻለው:

- ♣ የግል ንፅህና በመጠበቅ
- ♣ አከባቢን በማፅዳትና ቆሻሻዎችን በየቦታዉ ባለመጣል
- ♣ ስለታም ነገሮችን በጋራ ባለመጠቀምና የመሳሰሉት ናቸዉ።

### መልመጃ 2.4

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።**

1. ለሌሎች ሀላፊነት ለመዉሰድ የግል ንፅህናን መጠበቅ ያስፈልጋል።
2. ለሌሎች ጤና ሀላፊነት ለመዉሰድ አካባቢያችንን ማፅዳት አለብን።

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ።**

1. ____________ለሌሎች ጤና ሀላፊነት መዉሰድ ነዉ።

   ሀ. የግል ንፅህና መጠበቅ    ሐ. የቤት ንፅህና መጠበቅ

   ለ. አከባቢን ማፅዳት    መ. ሁሉም

2. የግል ጤናን ያለመጠበቅና ቆሻሻን በየቦታ መጣል -----

   ሀ. የሌላን ጤና ይጎዳል    ሐ. ለበሽታ ያጋልጣል

   ለ. የሌላን ጤና ይጠብቃል    መ. ሀ ና ሐ መልስ ናቸዉ።

## 2.5. በአካባቢ ዉስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች



*መታወቅ የሚገባቸው ቃላት*

- ➔ ቁሳቁስ
- ➔ አካባቢ

### የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ♦ በቤትና በትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ትዘረዝራላችሁ።

- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ትለያላችሁ፡፡
- በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ጥቅም ታብራራላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

2.5.1. በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ምንነት
2.5.2. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች
2.5.3. በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ጥቅም

## 2.5.1. በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ምንነት

### ተግባር 2.5.1 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:** በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች መዘርዘር

**መመሪያ:** በቡድን በመወያየት ሃሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

**ጥያቄ:** በአካባቢ ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች ምንድናቸዉ?

ውድ ልጆች! በአካባቢያችሁ ውስጥ ያሉትን ቁሳቁሶች ልትነግሩን ትችላላችሁ?

የአካባቢ ቁሳቁሶች በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ በብዛት ወይም በጥቂቱ ሊገኙ የሚችሉ ሀብቶች ናቸው፡፡

እንዲሁም አስፈላጊ ንጥረ ነገር ለማምረት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ፡፡

ሆኖም እነዚህ ቁሳቁሶች በአንዳንድ አካባቢዎች በብዛት ሊኖሩ ይችላሉ ነገርግን በሌላ ቦታ ላይገኙ ይችላሉ፡፡

በአካባቢያችን ውስጥ የተለያዩ ቁሳቁሶች ይገኛሉ፡፡

እነዚህም፡- አበቦች፣ ድንጋይ፣ አፈር፣ ሳር፣ ዛፎች፣ ብረት የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡



ስዕል 2.18 በአካባቢ ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች

## 2.5.2. በአካባቢ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች

### ተግባር 2.5.2 የጥንድ ውይይት

**ዓላማ:** በአካባቢ ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች መለየት

**መመሪያ:** በቡድን በመወያየት ሃሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ::

**ጥያቄ:** 1. በአካባቢ ውስጥ ያሉ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶችን ለይታችሁ ግለፁ::



ስዕል 2.19 በአካባቢ ውስጥ ያሉ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች

### የተፈጥሮ ቁሳቁስ

የተፈጥሮ ቁሳቁስ ከተፈጥሮ የተገኙትን ቁሳቁሶች ያመለክታል፡፡

የተፈጥሮ ቁሳቁስ ማለት ሰዉ ሊሰራዉ የማይችለዉ በተፈጥሮ ብቻ የሚገኝ ማለት ነዉ፡፡

ለምሳሌ እንጨት፣ ድንጋይ፣ ዉሃ፣ ዛፍ፣ አፈር፣ ቅጠላቅጠል ወዘተ...

### ሰው ሰራሽ ቁሳቁስ

ሰው ሰራሽ ቁሳቁስ በሰዎች የሚሠሩ ናቸው፡፡ አንድ ነገር ሰው ሰራሽ ከሆነ በአካባቢያችን በተፈጥሮ የማይገኝ ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ:- ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ብርጭቆ እና ሞባይል ስልኮች የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 2.5.3. በአካባቢ ዉስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ጥቅም

### ተግባር 2.5.3 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡** በአካባቢ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶች ጥቅም ማብራራት

**መመሪያ፡** በቡድን በመወያየት ሃሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

**ጥያቄ፡** 1. በአካባቢ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶች ጥቅም አብራሩ፡፡





ስዕል 2.20 በአካባቢ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶች ጥቅም

በአካባቢ ዉስጥ ያሉ ቁሳቁሶች አካባቢን ለማሻሻል፣ የተለያዩ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እና በቂ የቁሳቁስ አቅርቦትን ለማግኘት ይረዳሉ፡፡

ለምሳሌ የተፈጥሮ ቁሳቁስሶች፡-

ድንጋይ- ለቤት ግንባታ

አፈር- ዕፅዋቶችን ለማብቀል ወይም ለእርሻ ስራ

ዉሃ- ለመጠጣት፣ ንፅህናን ለመጠበቅ እና ለተክሎች ዕድገት ይጠቅማል፡፡

ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች ለምሳሌ፡-

ወንበር- ለመቀመጫ

ሞባይል ስልክ- መልዕክት ለማስተላለፍ ብርጭቆ- ዉሃ ለመጠጣት ይጠቅማል፡፡

## መልመጃ 2.5

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. ድንጋይ የተፈጥሮ ቁሳቁስ ነዉ፡፡
2. ከተፈጥሮ ቁሳቁሶች ዉሃ ለመጠጥ ያገለግላል፡፡

**ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ከሚከተሉት መካከል ሰዉ ሰራሽ ቁስ የሆነዉ የቱ ነዉ
   ሀ. ወንበር
   ለ. ድንጋይ
   ሐ.አፈር
   መ. ዛፍ

2. ከተፈጥሮ ቁሳቁስ ድንጋይ ለምን ይጠቅማል
   ሀ. ለዉበት
   ለ. ለግንባታ
   ሐ. ለእርሻ
   መ. ሁሉም

## 2.6. ብርሃን ምንድነዉ?

### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ብርሃን
- ጨለማ
- ማየት

### የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የብርሃን ጥቅም ትዘረዝራላችሁ::
- ጨለማ የብርሃን ያለመኖር መሆኑን ትገነዘባላችሁ::

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

2.6.1 የብርሃን ምንነትና ጥቅም
2.6.2 ብርሃንና ጨለማ



### 2.6.1. የብርሃን ምንነትና ጥቅም

**ተግባር 2.6.1 የጥንድ ውይይት**

**ዓላማ:** የብርሃንን ጥቅም መዘርዘር

**መመሪያ:** በጥንድ በመወያየት ሃሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ::

**ጥያቄ:** ብርሃን ለምን ይጠቅማል?

ስዕል 2.21 የሚበራ ባትሪ

ብርሃን ነገሮችን ለመለየት ወይም ለማየት ይጠቅማል፡፡

ብርሃን ቀለማትን ለመለየት ይጠቅማል፡፡

በአካባቢያችን የተለያዩ የብርሃን ምንጮች ይገኛሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ፀሐይ፣ ሻማ፣ አምፖል፣ ባትሪ ወዘተ…


## 2.6.2. ብርሃንና ጨለማ

### ተግባር 2.6.2 የጥንድ ዉይይት

**ዓላማ፡-** ጨለማና ብርሃንን መለየት

**መመሪያ፡-** በጥንድ ሆናችሁ ስለ ጨለማና ብርሃን ልዩነት በመወያየት የደረሳችሁበትን ውጤት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ጥያቄ፡-** የብርሃንና ጨለማ ልዩነት ምንድነዉ?







ስዕል 2.22 ላይ ምን ታያላችሁ?

በብርሃን ነገሮችን በማየት መለየት ይቻላል፡፡ በጨለማ ምንም ነገር ማየት አይቻልም፡፡

በአካባቢያችን ያሉት ቀለማት በብርሃን ብቻ ይታያሉ ወይም ይለያሉ፡፡

### መልመጃ 2.6

**ትዕዛዝ 1፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. ቀለማትን በጨለማ መለየት ይቻላል፡፡

2. ፀሐይ ብርሃንን ያመነጫል፡፡

**ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ____________የብርሃን ምንጭ ነዉ፡፡

   ሀ. ሳንቲም　　　　ሐ. ጠረጴዛ

   ለ. ባትሪ　　　　መ. መልስ የለም

2. በጨለማ___________ለየት ያስቸግራል፡፡

   ሀ. ቀለም　　　　ሐ. ሽታ

   ለ. ድምፅ　　　　መ. ሁሉም

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጭንቅላት ወይም ራስ፣ ፀጉር፣ ጆሮ፣ አይን፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ እጅ፣ ጣት፣ ደረት፣ ሆድ፣ እግር፣ ጉልበትና ቁርጭምጭሚት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ጥንቃቄ ካልተደረገ ለተለያዩ አደጋዎች ይጋለጣሉ፡፡

**የስሜት ሕዋሳት የምንላቸው:-**

- ዓይን
- አፍንጫ
- እጅ
- ምላስ ናቸዉ
- ጆሮ

**እነዚህም የሚሰጡት ጠቀሜታ:-**

- አይን ለማየት
- ጆሮ ለመስማት
- ምላስ ለመቅመስ
- አፍንጫ ለማሽተት
- እጅ ለመዳሰስ የሚያገለግሉን የስሜት ሕዋሶቻችን

ናቸው፡፡

## የአካል ክፍሎችን ንፅሕና ለመጠበቅ:-

- ♣ እጅን፣ ፊትንና ገላን በየጊዜው መታጠብ::
- ♣ ፀጉርን መታጠብና ማበጠር::
- ♣ ጥርስን በዘመናዊ ወይም በባህላዊ መፋቂያ ማፅዳት::
- ♣ ጥፍርን መቁረጥ::
- ♣ አፍንጫን በመሀረብ ወይም በንፁህ ጨርቅ ማፅዳት::
- ♣ እግርን በየዕለቱ በሳሙናና በውሃ መታጠብ::

ብርሃን ነገሮችን ለመለየት ወይም ለማየት ይጠቅማል:: በብርሃን ነገሮችን በማየት መለየት የሚቻል ሲሆን በጨለማ ግን ምንም ነገር ማየት አይቻልም::

## የምዕራፍ ሁለት የማጠቃለያ መልመጃዎች

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ::**

1. ጨውንና ስኳርን በጣዕማቸው መለየት እንችላለን::
2. መፀዳጃ ቤት ንፅሕናው ካልተጠበቀ መጥፎ ሽታ አለው::
3. እጅ የስሜት ህዋሳት ነዉ::
4. ጆሮ ለማየት ይጠቅማል::

**ትዕዛዝ 2:- የሚከተሉትን የስሜት ሕዋሳት ከጥቅማቸው ጋር በማስመር አገናኙ /አዛምዱ/::**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዓይን | ሀ. ለመዳሰስ |
| 2. አፍንጫ | ለ. ለማየት |
| 3. ጆሮ | ሐ. ለማሽተት |
| 4. እጅ | መ. ለመቅመስ |
| 5. ምላስ | ሠ. ለመስማት |

**ትዕዛዝ 3፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡**

1. መጥፎ ሽታ ያለው የትኛው ነው?
   - ሀ. አበባ
   - ለ. ሰንደል
   - ሐ. የሞተ እንስሳ
   - መ. ሁሉም
2. የስልክ መልዕክት የምንቀበለው በየትኛው የስሜት ሕዋሳችን ነው?
   - ሀ. በጆሮ
   - ለ. በዓይን
   - ሐ. በአፍንጫ
   - መ. ሁሉም
3. ብርሃን አመንጪ የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ድንጋይ
   - ለ. መስታወት
   - ሐ. ሻማ
   - መ. ሁሉም

# ምዕራፍ ሶስት

# የተፈጥሮ አካባቢ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- ሞቃትና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታዎችን ትለያላችሁ::
- ህይወት ያላቸዉ ነገሮችን ባህሪያት ታብራራላችሁ::
- ህይወት ያላቸዉና ህይወት የሌላቸዉ ነገሮችን ትለያላችሁ::
- ለምግብ፣ ለመጓጓዣና ለቤት ዉስጥ አጫዋችነት የሚያገለግሉ የቤት እንስሳትን በዝርዝር ትለያላችሁ::
- እንስሳትን ከሚያሳዩ ባህሪያት አንፃር ትመድባላችሁ::
- በአካባቢያችን ውስጥ ያሉ አስፈላጊ ዕፅዋቶችን ታብራራላችሁ::
- የቤት ውስጥ ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ በመጠቀም የግል የመፀዳጃ ንፅህና አጠባበቅን ትተገብራላችሁ::

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የተፈጥሮ አካባቢ በሚል ርዕስ የአካባቢ የአየር ሁኔታ፣ ህይወት ያላቸዉ ነገሮች ባህሪያት፣ የእንስሳት ምደባና በአካባቢያችን ያሉ እንስሳትና በአካባቢያችን ውስጥ ያሉ አስፈላጊ ዕፅዋቶች እንዲሁም ንፅህና እና ቆሻሻን ማስወገድና ሀገር በቀል የንፅህና አጠባበቅ ናቸዉ።

### በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

3.1 የአካባቢያችን አየር ሁኔታ
3.2 በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት ያላቸዉ ነገሮች
3.3 ንፅህናና የግል ንፅህና

## 3.1. የአካባቢያችን አየር ሁኔታ



**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- የአየር ሁኔታ
- ሞቃት
- ቅዝቃዜ
- ደረቅ

### ከንዑስ ርዕስ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- የአካባቢ የአየር ሁኔታዎችን ታብራራላችሁ።
- ሞቃትና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታዎችን ትለያላችሁ።
- የአካባቢ አየር ሁኔታዎችን ትዘረዝራላችሁ።

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

3.1.1 የአካባቢ አየር ሁኔታ
3.1.2 ሞቃትና ቅዝቃዜ

## 3.1.1. የአካባቢ አየር ሁኔታ

### ተግባር 3.1.1 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** የአካባቢ አየር ሁኔታ ማብራራት

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ::

**ጥያቄ:-** የአካባቢ አየር ሁኔታ ምንድነው?

### የአካባቢ የአየር ሁኔታ

የአየር ሁኔታ በአካባቢ አየር ውስጥ የአጭር ጊዜ ለውጦችን የሚያመለክት ነዉ::

የአየር ሁኔታ አማካይ የዕለት ተዕለት የአየር ሁኔታ ሲሆን የአካባቢን የአጭር ጊዜ ሁኔታዎችን ያንፀባርቃል::

የአካባቢ የአየር ሁኔታዎች የሚባሉት ዉርጭ፣ ሙቀት፣ ቅዝቃዜና ዝናብ የመሳሰሉት ናቸው::

በእነዚህ ጊዜያት ዉስጥ ቀንና ሌሊት ይፈራረቃሉ:: ይኸዉም አስራ ሁለት ሰዓት ቀን እና አስራ ሁለት ሰዓት ሌሊት ይሆናል::

ቀስተ-ደመና እና ጎርፍ ወቅታዊ የተፈጥሮ ክስተቶች ሲሆኑ ከአየር ሁኔታ ጋር በተያያዘ በአጋጣሚ የሚፈጠሩ ናቸው::



ስዕል 3.1 የአካባቢ የአየር ሁኔታ

## 3.1.2. ሞቃትና ቅዝቃዜ

### ተግባር 3.1.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** ሞቃትና ቅዝቃዜ የአየር ሁኔታን መግለፅ

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ።

**ጥያቄ:-** 1. ሞቃትና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታዎችን ልዩነት አብራሩ።

2. መጠነ-ሙቀትና የዝናብ ስርጭትን የሚያሳይ የንድፍ ካርታ በመሳል የአየር ሙቀትና የዝናብ ስርጭትን አሳዩ።

ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ማለት ጊዜያዊና ያልተለመደ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ነዉ።

በበጋ ሞቃታማ አየር ይከሰታል።

ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ማለት ጊዜያዊና ያልተለመደ ከፍተኛ ቅዝቃዜ የሚታይበት የአየር ሁኔታ ነዉ።

በክረምት ቀዝቃዛ አየር ይከሰታል።

### መልመጃ 3.1

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።**

1. በዝናባማ ወቅት ከፍተኛ የሆነ ቅዝቃዜ ይታያል።
2. በጋና ክረምት የአየር ሁኔታ አይነቶች ናቸዉ።

**ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ።**

1. ቀዝቃዛ አየር በየትኛዉ ወቅት በብዛት ይከሰታል?

   ሀ. በበጋ ለ. በክረምት ሐ. በሁለቱም

2. በበጋ-------- በብዛት ይኖራል።

   ሀ. ሙቀት ለ.ዝናብ ሐ. ቅዝቃዘ መ. ሁሉም

## 3.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች

**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ህይወት
- አመጋገብ
- ዱር
- እንስሳት
- መተንፈስ
- ዕፅዋት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ህይወት ያላቸዉን ነገሮች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- እንስሳትን በቆዳ ሽፋናቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው እና በእግራቸው ብዛት ትመድባላችሁ፡፡
- የቤት እንስሳትን ጥቅም ትናገራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ እንስሳትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ያሉ አስፈላጊ ዕፅዋትን ትለያላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ያሉ አስፈላጊ ዕፅዋትን ጥቅም ታብራራላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

3.2.1 ህይወት ያላቸው ነገሮች ባህሪያት
3.2.2 የእንስሳት ምድብ
3.2.3 የቤት እንስሳት ጥቅም
3.2.4 በአካባቢያችን ያሉ እንስሳትና ወቅታዊነታቸው
3.2.5 በአካባቢያችን ያሉ ዕፅዋትና ጥቅሞቻቸዉ

### 3.2.1. ህይወት ያላቸው ነገሮች ባህሪያት


**ተግባር 3.2.1 የቡድን ውይይት**

ዓላማ:- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮችን ባህሪያት ማብራራት

*መመሪያ:-* በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ::

ጥያቄ:- 1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች ባህሪያት ስዕል በመሳል አሳዩ::

ውድ ልጆች! ከዚህ በታች በስዕል የቀረቡትን ህይወት ያላቸዉ ነገሮችን በማየት ስማቸዉን ዘርዝሩ::



ስዕል 3.2 ህይወት ያላቸዉ ነገሮች

ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሁለት ይመደባሉ:: እነሱም:-

1. እፅዋት
2. እንስሳት

ውድ ልጆች! ከዚህ በታች በስዕል የሚታዩትን እንስሳቶች ስማቸዉን ጥቀሱ::



ስዕል 3.3 እንስሳት

እንስሳት የምንላቸዉ ጦጣ፣ ድኩላና ዓሳ ወዘተ...ናቸዉ።

ዉድ ልጆች! ከዚህ በታች በስዕል የሚታዩ እፅዋት ምንድናቸዉ?




ስዕል 3.4 እፅዋት

እፅዋት የሚባሉት እንሰት፣ ቡና፣ ጎመን ወዘተ...

## ሕይወት ያላቸው ነገሮች ባህሪያት

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይንቀሳቀሳሉ፣ ይመገባሉ፣ ይተነፍሳሉ፣ ይዋለዳሉ ወዘተ...




ስዕል 3.5 ህይወት ያላቸው ነገሮች እንቅስቃሴ

### ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ?

ህይወት ያላቸው ነገሮች ይንቀሳቀሳሉ።

ለምሳሌ ወፎች ይበራሉ ሌሎች እንስሳት ይራመዳሉ፡፡






ስንጥብ-የዓሳ መተንፈሻ አካል
ሳንባና አፍንጫ የሰው መተንፈሻ አካል

ስዕል 3.6 ህይወት ያላቸው ነገሮች ሲተነፍሱ

ህይወት ያላቸው ነገሮች ይተነፍሳሉ፡፡

የእንስሳት የመተንፈሻ አካላት ሳንባ፣ አፍንጫ፣ ስንጥብ የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ስዕል 3.7 የእንስሳትና የዕፅዋት ዕድገት


ዉድ ልጆች! ከላይ ስዕሉ ምን ያሳያል? የተመለከታችሁትን ለመምህራችሁ ግለፁ።


ህይወት ያላቸው ነገሮች ያድጋሉ።

ለምሳሌ፡- ጥጃ አድጎ በሬ ይሆናል፣ ችግኝ ዛፍ ይሆናል እንዲሁም ጫጩት ዶሮ ይሆናል።









ስዕል 3.8 ህይወት ያላቸው ነገሮች ሲዋለዱ

ከላይ ካለዉ ስዕል ምን ተረዳችሁ?

ከስዕል 3.8 ላይ እንደተመለከታችሁት የሰዉ ልጅ፣ ወፎች፣ እንዲሁም ከብቶች ይዋለዳሉ። ስለዚህ ህይወት ያላቸው ነገሮች ይዋለዳሉ።







ስዕል 3.9 ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሲመገቡ

ዉድ ልጆች! ከዚህ በላይ በስዕሉ ላይ ምን ተመለከታችሁ?

ከዚህ በላይ በስዕሉ ላይ እንደተመለከታችሁት ቤተሰብ ምግብ ሲመገቡ፣ ዶሮ ጥሬ ስትለቅም እና ዉሻ አጥንት ስጊጥ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይመገባሉ፡፡

በአከባቢያችሁ የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው፡፡ እነሱም:-

ሀ. ይመገባሉ
ለ. ይተነፍሳሉ
ሐ. ያድጋሉ
መ. ይንቀሳቀሳሉ
ሠ. ይዋለዳሉ
ረ. ይፀዳዳሉ

## 3.2.2. የእንስሳት ምድብ


### ተግባር 3.2.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ**:- እንስሳትን መመደብ

**መመሪያ**:- በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡


**ጥያቄ**:- እንስሳትን በባህሪያቸዉ እንዴት መመደብ ይቻላል?

ዉድ ልጆች! ከታች በስዕሉ ላይ የምትመለከቷቸውን እንስሳት በስም ዘርዝሩ፡፡



ስዕል 3.10 የቤት እንስሳት

ዉድ ልጆች! ከታች በስዕሉ ላይ የምትመለከቷቸውን እንስሳት ስም ጥቀሱ::







ስዕል 3.11 የዱር እንስሳት

በአከባቢያችን የሚገኙ እንስሳት በሁለት ይመደባሉ:-

1. የቤት እንስሳት
2. የዱር እንስሳት

የቤት እንስሳት የሚባሉት ላም፣ በግ፣ ዶሮ፣ ድመት፣ ዉሻ፣ አህያ እና የመሳሰሉት ናቸው::

የዱር እንስሳት የሚባሉት አንበሳ፣ ጉሬዛ፣ የሜዳ አህያ እና የመሳሰሉት ናቸው::

## የእንስሳት ምድብ በባህሪያቸው

እንስሳት በሚያሳዩት ባህሪያት የተለያዩ ምድብ ሊኖራቸው ይችላል::

ለምሳሌ:-

ሀ. በቆዳ መሸፈኛቸው
ለ. በእንቅስቃሴያቸው
ሐ. በእግር ብዛታቸው



በፀጉር የተሸፈነ



በላባ የተሸፈነ



በቅርፊት የተሸፈነ


ስዕል 3.12 እንስሳት በቆዳ መሸፈኛቸው

ዉድ ልጆች! ከላይ ስዕል 3.12 ከምትመለከቷቸው እንስሳት ውጪ ሌሎች በአካባቢያችሁ የሚገኙት እንስሳትን መድቧቸዉ።

## እንስሳት በቆዳ መሸፈኛቸው በሶስት ይመደባሉ

- አጥቢ እንስሳት ቆዳቸው በፀጉር የተሸፈነ ነው።
- ወፎች ቆዳቸው በላባ የተሸፈነ ነው።
- ተሳቢ እንስሳት ቆዳቸው በቅርፊት የተሸፈነ ነው።

ዉድ ልጆች! ከዚህ በታች በስዕሉ ላይ የምታይዋቸው እንስሳት ምንድናቸው? በየትኛው ምድብ ይገኛሉ?




ስዕል 3.13 እንስሳት በእንቅስቃሴያቸዉ

## እንስሳት በእንቅስቃሴያቸው በሶስት ይመደባሉ

- በምድር ላይ በእግራቸው የሚንቀሳቀሱ
- በደረት የሚሳቡ
- በውሃ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ



ስዕል 3.14 ሀ. አራት እግር ያላቸዉ

ስዕል 3.14 ለ. ሁለት እግር ያላቸዉ

ዉድ ልጆች! ከላይ በስዕሉ ላይ ያሉ እንስሳት ምንድናቸው?

እንስሳት በእግር ብዛት በሁለት ይመደባሉ፡፡

1. በአራት እግር የሚንቀሳቀሱ
2. በሁለት እግር የሚንቀሳቀሱ

## 3.2.3. የቤት እንስሳት ጥቅም

### ተግባር 3.2.3 የቡድን ውይይት


**ዓላማ፡-** የቤት እንስሳትን ጥቅም መዘርዘር

**መመሪያ፡-** በቡድን በመሆን የተወያያችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ጥያቄ፡-** የቤት እንስሳት ለምን ይጠቅማሉ?

ከዚህ በታች ከምትመለከቷቸው ስዕሎች ምን ተገነዘባችሁ?

ስዕሎቹ ላይ ያሉት ነገሮች ለምን ይጠቅማሉ? ሀሳባችሁን ለመምራችሁ ተናገሩ?



ስዕል 3.15 የእንስሳት ጥቅም ለምግብነት

ከዚህ በታች ከምትመለከቷቸው ስዕሎች ምን ተረዳችሁ? ሀሳባችሁን ለመምራችሁ ተናገሩ?



ስዕል 3.16 እንስሳት ለመጓጓዣነት

ከዚህ በታች ከምትመለከቷቸው ስዕሎች ምን ተረዳችሁ? ሀሳባችሁን ለመምራችሁ ተናገሩ?



ስዕል 3.17 እንስሳት ለመጫወቻነትና ለጥበቃ

### የቤት እንስሳት ጥቅም

ለምግብነት የሚያገለግሉ የቤት እንስሳት:-

በሬ፣ ላም፣ ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል ወዘተ... ናቸው

ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ የቤት እንስሳት:-

ፈረስ፣ አህያ እና በቅሎ ናቸው።

ለቤት ውስጥ ጥበቃና አጫዋችነት የሚያገለግሉ የቤት እንስሳት ድመት እና ውሻ ናቸው።

## 3.2.4. በአካባቢያችን ያሉ እንስሳት

### ተግባር 3.2.4 የማስተዋል ጥያቄ

**ዓላማ:-** በአካባቢያችን ያሉ እንስሳት መዘርዘር

**መመሪያ:-** በቡድን በመሆን የተወያያችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ:-** 1. በአካባቢያችን ያሉ እንስሳትን ዘርዝሩ።


ልጆች! በአካባቢያችሁ ያሉትን እንስሳት ልትነግሩን ትችላላችሁ?

በአካባቢያችን የተለያዩ እንስሳቶች ይገኛሉ።

እነዚህም የቤትና የዱር እንስሳት ተብለዉ በሁለት ይከፈላሉ።

የቤት እንስሳት የሚባሉት:- በሬ፣ ላም፣ ፈረስ፣ በግ፣ ፍዬል እና የመሳሰሉት ናቸዉ።

የዱር እንስሳት የሚባሉት:- አንበሳ፣ ነብር፣ ጎሽ፣ ጅብ፣ ዝንጀሮ፣ ዝሆን፣ የሜዳ አህያ የመሳሰሉት ናቸዉ።



ስዕል 3.18 በአካባቢያችን ያሉ እንስሳት

## 3.2.5. በአካባቢያችን ያሉ አስፈላጊ ዕፅዋትና ጥቅሞቻቸዉ


### ተግባር 3.2.5 የቡድን ውይይት

ዓላማ፡- በአካባቢ የሚገኙ ዕፅዋትን መዘርዘር

መመሪያ፡- በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

ጥያቄ፡-1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አስፈላጊ ዕፅዋት ስማቸውን ዘርዝሩ::

2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አስፈላጊ ዕፅዋት ጥቅም አብራሩ::




ስዕል 3.19 በአካባቢያችን የሚገኙ አስፈላጊ ዕፅዋት

ከላይ በስዕል 3.19 የምትመለከቱትን ዕፅዋት ስም ጥቀሱ

በአካባቢያችን የሚገኙ አስፈላጊ ዕፅዋት የምንላቸው፡-

በቆሎ፣ እንሰት፣ ድንች፣ ጤና አዳም፣ ዳማከሴ፣ ባህር ዛፍ፣ ዋንዛ የመሳሰሉት ናቸው::

## በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋት ጥቅም



ስዕል 3.20 ሀ. ለምግብነት የሚያገለግሉ ዕፅዋት



አጠና ወይም ፍልጥ



ጎጆ ቤት



ቆርቆሮ ቤት

ስዕል 3.20 ለ. ዕፅዋት ለአጠናና ለቤት መስሪያ



ጉሬዛዎች በዛፍ ላይ



አናብስት በጫካ



አዕዋፍት ዛፍ ላይ

ስዕል 3.20 ሐ. ዕፅዋት ለእንስሳት መጠለያነት



ስዕል 3.20 መ. ዕፅዋት ለልብስ መስሪያነት



ሬት



ጤና አዳም



ሞሪንጋ ወይም ሽፈራው

ስዕል 3.20 ሠ. ዕፅዋት ለመድሀኒትነት

በአጠቃላይ በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋት ጥቅም

- ለምግብነት
- ለልብስ መስሪያነት
- ለመጠለያነት
- ለመድሐኒትነት

## መልመጃ 3.2

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. አፈር ህይወት ያለው ነገር ነው፡፡
2. ጥቅል ጎመን ለምግብነት አያገለግልም፡፡___
3. ህይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ ያድጋሉ፡፡
4. ድመት የቤት እንስሳ አይደለም፡፡

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ሁለት እግር ያለው የቤት እንስሳ የቱ ነው?

   ሀ. ዶሮ  ሐ. በግ

   ለ. ፍየል  መ. በሬ

2. የዱር እንስሳ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አንበሳ  ሐ. ጦጣ

   ለ. ዝንጀሮ  መ. ሁሉም

3. ለመጓጓዣነት የሚያገለግለው የቤት እንስሳ__ይባላል፡፡

ሀ. በሬ  
ሐ. ላም  
ለ. በቅሎ  
መ. ፍየል

4. ____________በአካባቢ የሚገኝ አስፈላጊ ዕፅዋት ነዉ፡፡

ሀ. አተር  
ሐ. በቆሎ  
ለ. ስኳር ድንች  
መ. ሁሉም

## ትዕዛዝ 3፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

1. ህይወት ያላቸው ነገሮች በስንት ይመደባሉ? ዘርዝሩ፡፡
2. እንስሳት ወቅቶች ሲቀያየሩ ምን ዓይነት ፀባይ ያሳያሉ? በምሳሌ አብራሩ፡ ፡
3. ዕፅዋት ለምን ይጠቅማሉ?
4. የእንስሳትን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡

## 3.3. ንፅህናና የግል ንፅህና

### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ደጅ
- መታጠብ
- ንፁህ
- ማፅዳት
- ንፅህና አጠባበቅ
- ቆሻሻ ማስወገድ

### ከንዑስ ርዕስ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የቤት ውስጥ ንፅህና መጠበቂያ እቃዎችን በመጠቀም የግል ንጽህና አጠባበቅን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- የቆሻሻ አወጋገድን ታብራራላችሁ፡፡
- ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያዎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች


3.3.1. ንፅህና አጠባበቅ
3.3.2. የቆሻሻ ማስወገድ
3.3.3. ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ አጠቃቀም

## 3.3.1. ንፅህና አጠባበቅ

### ተግባር 3.3.1 የማስተዋል ጥያቄ

**ዓላማ:-** የቤት ውስጥ ንፅህና መጠበቂያ እቃዎችን በመጠቀም የግል ንጽህና አጠባበቅን ማስረዳት

**ጥያቄ:-** የቤት ውስጥ ንፅህና መጠበቂያ እቃዎች ምንድናቸው? እንዴት መጠቀም ይቻላል?



ስዕል 3.21 የቤት ዉስጥ ንፅህና



ስዕል 3.22 ልጆቹ ምን እየሰሩ ነው?



ስዕል 3.23 ቤት ሲያፀዱ



ስዕል 3.24 የቤት ዕቃ ሲታጠብ




ስዕል 3.25 የአካባቢና የመፀዳጃ ቤት ንፅህና አጠባበቅ

## የንፅህና አጠባበቅ የሚባሉት:

- የግል ንፅህና መጠበቅ
- የቤት ንፅህና መጠበቅ
- የቤት ዉስጥ ዕቃዎች ንፅህና መጠበቅ
- የአከባቢ ንፅህና መጠበቅና
- የመፀዳጃ ቤት ንፅህና መጠበቅ ናቸዉ::

## 3.3.2. የቆሻሻ አወጋገድ

### ተግባር 3.3.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** የቆሻሻ አወጋገድን ማስረዳት

**መመሪያ:-** በቡድን ሆናችሁ በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ::

**ጥያቄ:-** 1. ቆሻሻ ማስወገድ ማለት ምን ማለት ነዉ?

2. ቆሻሻዎች እንዴት ከአካባቢ ማስወገድ ይቻላል?





ስዕል 3.26 የቆሻሻ አወጋገድ

ቆሻሻን ከአካባቢ ማስወገድ ለጤና ይጠቅማል::

ስለዚህ ቆሻሻዎችን ከአካባቢያችሁ በመሰብሰብ ማስወገድ አለባችሁ::

ከአካባቢ የተወገዱ ቆሻሻዎች በማቃጠልና የቆሻሻ ጉድጓድ ዉስጥ መጣል ያስፈልጋል::

ቆሻሻ አወጋገድ ስርኣት በየአካባቢዉ ይለያያል::

የከብቶች እበት፣ የበግና የፍየል በጠጥ እና የዶሮ ኩስ መሰብሰብ ኮምፖስት ወይም ፍግ ለማዘጋጀት አንድ ቦታ ላይ ይሰበሰባል::

## 3.3.3. ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አጠቃቀም

### ተግባር 3.3.3 የቡድን ውይይት

**ዓላማ:-** ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ መዘርዘር

**መመሪያ:-** በቡድን በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርቡ::

**ጥያቄ:-** 1. ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ::

ልጆች! በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ታዉቃላችሁ?

ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ የሚንላቸዉ ከአካባቢያችን በቀላሉ ልናገኝ የምንችላቸዉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ናቸዉ::

ለምሳሌ:- እንዶድ፣ ልምጭና አመድ የመሳሰሉት ናቸዉ::

እንዶድ ልብስ ለማፅዳት ይጠቅማል::

ልምጭ ጥርስ ለማፅዳት ይጠቅማል::





ስዕል 3.27 ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች

## መልመጃ 3.3

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ::**

1. ቆሻሻን ማስወገድ ለጤና አስፈላጊ ነዉ::
2. የቤት ንፅህና መጠበቅ አያስፈልግም::
3. እንዶድ ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ቁስ ነዉ::

**ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ::**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የቤት ውስጥ የንፅህና መጠበቂያ እቃ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ሳሙና ለ. መወልወያ ሐ. መጥረጊያ

መ. ሁሉም

2. የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ የሚባለው የቱ ነው?

ሀ. ደጅ ማፅዳት ሐ. ቆሻሻ ማቃጠል

ለ. መንገድ መጥረግ መ. ሁሉም

3. የግል ንፅህና አጠባበቅን የሚያመለክተው የቱ ነው?

ሀ. ፊት መታጠብ ሐ. ገላን መታጠብ

ለ. ጥርስ መቦረሽ መ. ሁሉም

4. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ነው?

ሀ. ልም ሐ. ሳሙና

ለ. የጥርስ ብሩሽ መ. መልስ የለም

## የምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ

የአየር ሁኔታ በአካባቢ አየር ውስጥ የአጭር ጊዜ ለውጦችን የሚያመለክት ነዉ፡፡

የአካባቢ አየር ሁኔታ ማለት በጥቂት ሰዓታት ውስጥ የሚለዋወጥ የአየር ፀባይ ነው፡፡

የአየር ሁኔታ አካላት የሚባሉት የሙቀት መጠን፣ ንፋስ፣ እርጥበትና ደመና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ማለት ጊዜያዊና ያልተለመደ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ነዉ፡፡

በበጋ ሞቃታማ አየር ይከሰታል፡፡

ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ማለት ጊዜያዊና ያልተለመደ ከፍተኛ ቅዝቃዜ የሚታይበት የአየር ሁኔታ ነዉ፡፡

በክረምት ቀዝቃዛ አየር ይከሰታል፡፡

በአካባቢያችሁ የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች ይመገባሉ፣ ይተነፍሳሉ፣ ያድጋሉ፣ ይንቀሳቀሳሉ፣ ይፀዳዳሉ እንዲሁም ይዋለዳሉ፡፡

ህይወት ያላቸው ነገሮች እንስሳትና እፅዋት በመባል ይመደባሉ፡፡

በአካባቢያችን የተለያዩ እንስሳቶች ይገኛሉ፡፡

እነዚህም የቤትና የዱር እንስሳት ተብለዉ በሁለት ይከፈላሉ፡፡

እንስሳት ለምግብነት፣ ለመጓጓዣነት፣ ለቤት ጥበቃና ለቤት ዉስጥ አጫዋችነት ያገለግላሉ፡፡

በአካባቢያችን የሚገኙ አስፈላጊ ዕፅዋት የምንላቸው፡-

በቆሎ፣ እንሰት፣ ድንች፣ ጤና አዳም፣ ዳማከሴ፣ ባህር ዛፍ፣ ዋንዛ የመሳሰሉት ናቸው

በአጠቃላይ በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋት ጥቅም

- ለምግብነት
- ለመጠለያነት
- ለልብስ መስሪያነት
- ለመድሀኒትነት ወዘተ…

የግል፣ የቤትና የአካባቢ ንፅህና መጠበቅ ለጤና አስፈላጊ ነዉ፡፡

ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ የሚንላቸዉ ከአካባቢያችን በቀላሉ ልናገኝ የምንችላቸዉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ናቸዉ፡፡

ለምሳሌ፡- እንዶድ፣ ልምጭና አመድ የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## የምዕራፍ ሶስት የክለሳ መልመጃዎች

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. ህይወት ያላቸው ነገሮች አይንቀሳቀሱም፡፡
2. ፈረስ ለመጓጓዣነት ይጠቅማል፡፡
3. አንበሳ የቤት እንስሳ ነዉ፡፡
4. ዓሳ ዉሃ ዉስጥ ይኖራል፡፡
5. በክረምት ይሞቃል፡፡

## ትዕዛዝ 2፡- በ “ሀ” ሥር ለተዘረዘሩት ተስማሚያቸውን ከ “ለ” ስር ካሉት ጋር በማስመር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በደረት የሚሳብ | ሀ. የግል ንፅህና |
| 2. የዱር እንስሳ | ለ. እባብ |
| 3. የቤት እንስሳ | ሐ. ላም |
| 4. እጅ መታጠብ | መ. የአካባቢ ንፅህና |
| 5. መንገድ ሲጠረግ | ሠ. ዝንጀሮ |

## ትዕዛዝ 3፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡

1. እንስሳት ለምን ይጠቅማሉ?
   ሀ. ለምግብ ሐ. ለቤት ጥበቃ
   ለ. ለመጓጓዣ መ. ሁሉም
2. ከሚከተሉት ውስጥ የአየር ሁኔታ የሆነዉ የቱ ነው?
   ሀ. ቅዝቃዜ ሐ. ዉርጭ
   ለ. ሙቀት መ. ሁሉም
3. የዕፅዋት ጥቅም ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ለምግብነት ሐ. ለመድሐኒትነት
   ለ. ለመጓጓዣ መ. ሁሉም
4. ____________ ባለ አራት እግር የቤት እንስሳ ነው፡፡
   ሀ. ፈረስ ሐ. ፍዬል
   ለ. ላም መ. ሁሉም
5. ____________የአየር ሁኔታን አይወስንም፡፡
   ሀ. እርጥበት ሐ. ሙቀት
   ለ. ዛፍ መ. ንፋስ
6. ከሚከተሉት ውስጥ ሀገር በቀል የንፅህና መጠበቂያ ሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. እንዶድ ሐ. አመድ
   ለ. ልምጭ መ. ሁሉም

# ምዕራፍ አራት

# ማህበራዊ አካባቢ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የቤተሰቦቻችሁን አባላት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የቤተሰብ ሚና ትወያያላችሁ/ታብራራላችሁ፡፡
- የቤተሰቦቻችሁን መሠረታዊ ፍላጎቶች ትገልጻላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁን ግቢ ትለያላችሁ፡፡
- የአቻ ግንኙነታችሁንና በትምህርት ቤት ውስጥ ሊታከናውኗቸው የሚትችሏቸውን ተግባራት ታዳብራላችሁ፡፡
- የቤተሰቦቻችሁን አባላት መብትና ሀላፊነት ትወያያላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁንና አካባቢያችሁን በሚትጠቀሙበት ጊዜ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መሆኑን የሚሳይ ስዕል/ ፖስተር ትስላላችሁ፡፡

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

4.1 የቤተሰብ አባላትና ሚናዎቻቸው
4.2 ለመኖር ምን ያስፈልጋል?
4.3 በትምህርት ቤት ውስጥ ምን እናገኛለን?
4.4 በጋራ እንጫወት በጋራ እንስራ
4.5 የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎች

## መግቢያ

ዉድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የማህበራዊ አካባቢ ማለትም የቤተሰብ አባላት ዝርዝር፣ የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶች፣ የቤተሰብ መብትና ሀላፊነት፣ አካባቢና የትምህርት ቤት ግቢ እንዲሁም በጋራ መጫዎትና በጋራ መስራት የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎችን በተመለከተ በተገቢው ትማራላችሁ፡፡

# 4.1. የቤተሰብ አባላትና ሚናዎቻቸው

### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- የቤተሰብ አባላት
- መከባበር
- መልካም አርአያነት
- ሥነ ምግባር
- በስራ መረዳዳት
- ጥሩ አስተዳዳር

## የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች! ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የቤተሰቦቻችሁን አባላት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የቤተሰቦቻችሁን አባላት አኗኗር ሁኔታ ታብራራላችሁ፡፡
- የቤተሰብ ሀላፊነትና የስራ ድርሻ ትገልፃላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

4.1.1 የቤተሰብ አባላት
4.1.2 የቤተሰብ መረዳዳት

4.1.3 የቤተሰብ ሀላፊነትና የስራ ድርሻ

## 4.1.1. የቤተሰብ አባላት

### ተግባር 4.1.1 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** የቤተሰብ አባላትን መዘርዘር

**መመሪያ፡-** በጥንድ በመወያየት የቤተሰብ አባላትን ዝርዝር ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

**ጥያቄ፡-** 1. የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እነማን ናቸዉ?

2. ከእናንተ በፊት ቀድመው የተወለዱናከእናንተ በኋላ የተወለዱ ወንድም ወይም እህት ምን ተብሎ ይጠራሉ?



ስዕል 4.1 የቤተሰብ አባላት

የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እናት፣ አባት፣ እህቶች፣ ወንድሞች፣ አክስቶች፣ አጎቶች እና ሌሎችም የቅርብ ቤተሰቦች ናቸው፡፡

እናትና አባት የምንላቸዉ የልጆች ወላጆች እና የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች ናቸው፡፡

ሴት ልጆች እህት ሲባሉ ወንድ ልጆች ደግሞ ወንድም ይባላሉ፡፡

- የእናት ወይም የአባት ወንድም አጎት ይባላል፡፡
- የእናት ወይም የአባት እህት አክስት ትባላለች፡፡

ልጆች በዕድሜ ታናናሽ የሆኑ ልጆች ታላላቅ እህቶቻቸውንና ወንድሞቻቸውን ማክበር አለባቸው፡፡

## 4.1.2. የቤተሰብ መረዳዳት

### ተግባር 4.1.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** የቤተሰብ መረዳዳት ሁኔታን መግለፅ

**መመሪያ፡-** በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ጥያቄ፡-** 1. ለመኖር የቤተሰብ አባላት ምን ያደርጋሉ?

2. እናንተ ቤተሰቦቻችሁን በምን በምን ትረዳላችሁ?



ስዕል 4.2 ልጆች ቤተሰባቸውን በስራ ሲረዱ

አንድ ቤተሰብ ጥሩ መሆን የሚችለው በቤተሰብ አባላት **መካከል መልካም ግንኙነት ሲኖር** ነው፡፡

ቤተሰባዊ መልካም ግንኙነት የምንላቸው፡- መተሳሰብ፣ መግባባት፣ መፈቃቀር፣ መከባበር፣ በስራ መረዳዳት፣ ችግርን በጋራ መፍታትና ታማኝነት ናቸው፡፡

## 4.1.3. የቤተሰብ ሀላፊነትና የስራ ድርሻ

### ተግባር 4.1.3 የቡድን ውይይት

ዓላማ፡- የወላጆቻችሁን የስራ ድርሻ በሚና ጨዋታ ማሳየት

መመሪያ፡- የአባት፣ የእናትና የልጆችን የስራ ድርሻ በሚና ጨዋታ አሳዩ።

ጥያቄ፡- 1.የወላጆቻችሁ የስራ ድርሻ አንድ ዓይነት ነው? ለምን?

2. የስራ ድርሻቸው ምን ምን እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

ወላጆች በቤተሰባቸው ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም አለባቸው፡፡ ይኸውም ፡- መልካም አርአያነት፣ ጥሩ አስተዳደር፣ እንክብካቤና ፍቅር ናቸው።

መልካም አርአያነት: ወላጆች ለልጆቻቸው ጥሩ ነገር እየሰሩ ካስተማሩዋቸው መልካም አርአያነት ይባላል።





ስዕል 4.3 ወላጆች ለልጆቻቸው ሰርተው ሲያሳዩ

ጥሩ የቤተሰብ አስተዳደር ማለት ቤተሰብን በጥሩ ሁኔታ መምራት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ልጆችን መቆጣጠር፣ መምከርና የመሳሰሉት ናቸው።



ስዕል 4.4 የቤተሰብ አስተዳደር

ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ?

**እንክብካቤና ፍቅር** ማለት ወላጆች በአቅማቸው ልጆቻቸውን የሚረዱበት መንገድ ነዉ፡፡

ለምሳሌ፡- ሲታመሙ ማሳከም፣ ማስተማር፣ ደህንነታቸውን መጠበቅ ወዘተ...



ስዕል 4.5 ወላጆች ልጆቻቸውን ሲንከባከቡ

ከስዕል 4.12 ምን ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

## መልመጃ 4.1

**ትዕዛዝ 1፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. የቤተሰብ አባል የሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. አባት ለ. እናት ሐ. ልጅ መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ዉስጥ የቤተሰብ መልካም ግንኙነት መገለጫ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. መተሳሰብ ሐ. መከባበር

   ለ. መጣላት መ. ሁሉም

ትዕዛዝ 2፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

1. የአባት እህት ወይም የእናት እህት______________ ትባላለች፡፡
2. የአባት ወንድም ወይም የእናት ወንድም_________ ይባላል፡፡

## 4.2. ለመኖር ምን ያስፈልጋል?



መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ፀሐይ
- መጠለያ
- ዝናብ
- ብርድ
- ምግብ
- ልብስ

### የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የቤተሰቦቻችሁን መሠረታዊ ፍላጎቶች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የቤተሰቦቻችሁን መሠረታዊ ፍላጎቶች ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

4.2.1 የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች
4.2.2 የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች አስፈላጊነት

### 4.2.1. የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች

**ተግባር 4.2.1 የቡድን ውይይት**

ዓላማ፡- የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶችን መዘርዘር

መመሪያ፡- በቡድን በመወያየት የተረዳችሁትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ጥያቄ፡- 1. የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶችን አብራሩ፡፡

የአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች የምንላቸው ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ ናቸው።





ስዕል 4.6 ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች

## 4.2.2. የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ጥቅም

### ተግባር 4.2.2 የቡድን ውይይት

ዓላማ፡- የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ጥቅም መዘርዘር

መመሪያ፡-በቡድን በመወያየት ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ጥያቄ፡ የቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ምንድናቸው?





ስዕል 4.7 ምግብ

ከስዕሉ ላይ ምን ይታያችኋል?

በየአካባቢያችን የሚበቅሉና ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ይገኛሉ። እነዚህም፡- ጤፍ፣ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ እንሰት፣ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ የመሳሰሉት ናቸው።

ለምግብነት ከሚውሉ እንስሳት መካከል በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ላም የመሳሰሉት ናቸው ።

### የምግብ ጥቅም

- ♣ ጤንነታችንን ይጠብቃል፡፡
- ♣ የተስተካከለ አካላዊ ዕድገት እንዲኖረን ያግዛል፡፡
- ♣ ከባድና ቀላል ስራዎችን ለመስራት ይረዳናል፡፡





ስዕል 4.8 ልብስ

ዉድ ልጆች! በእናንተ አካባቢ የሚለበሱ የልብስ አይነቶችን ተናገሩ፡፡

የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች አሉ፤ እነሱም፡- ኮት፣ ጃኬት፣ ሱሪ፣ ሹራብ፣ ጋቢ፣ ሸሚዝ፣ ቡልኮ፣ ቀሚስ ወዘተ…

ልዩ ልዩ የልብስ አይነቶች ከተለያዩ ግብዓቶች ይሰራሉ፡፡

እነሱም፡- ከጥጥ፣ ከሱፍና ከቆዳ ናቸው፡፡

### የልብስ ጥቅም፡-

1. ከብርድ፣ ከፀሐይና ከዝናብ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡
2. ውበትን ለመጠበቅ እና ለማጌጥ ይጠቅማል፡፡





ስዕል 4.9 መጠለያ

### በየአካባቢያችሁ የሚገኙ የመጠለያ ዓይነቶችን ጥቀሱ

መጠለያ ለአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ መጠለያ

የምንላቸው ጎጆ ቤት፣ ቆርቆሮ ቤት እና አፓርታማ ቤቶች ናቸው።

መጠለያ ከዝናብ፣ ከፀሐይና ከአውሬ ለመከላከል ይጠቅማል።

### መልመጃ 4.3

**ትዕዛዝ 1፡- በ "ሀ" ሥር ለተዘረዘሩት ተስማሚያቸውን ከ "ለ" ስር ካሉት ጋር በመስመር አዛምዱ።**

| ሀ | | ለ |
|---|---|---|
| 1. | ምግብ | ሀ. ሽሚዝ፣ ኮት፣ ብርድ ልብስ |
| 2. | ልብስ | ለ. የሳር ክዳን ቤት፣ ቆርቆሮ ክዳን ቤት |
| 3. | መጠለያ | ሐ. ስጋ፣ እንጀራ፣ ድንች |

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ።**

1. የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎት የሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ምግብ ሐ. ልብስ
   ለ. መጠለያ መ. ሁሉም
2. ከሚከተሉት ዉስጥ የልብስ ጥቅም ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ከዝናብ ለመከላከል ሐ. ከአውሬ ለመከላከል
   ለ. ከፀሐይ ለመከላከል መ. ሁሉም

## 4.3. በትምህርት ቤታችን ውስጥ ምን እናገኛለን?



**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ሰንደቅ ዓላማ
- ቤተ-መጽሐፍት
- ቤተ-ሙከራ
- ማበልፀጊያ ማዕከል

### የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የትምህርት ቤታችሁን ግቢ ትለያላችሁ፡፡
- የአቻ ግንኙነታችሁንና በትምህርት ቤት ውስጥ ልታከናውኗቸው የሚትችሏቸውን ተግባራት ታዳብራላችሁ፡፡
- ትምህርት ቤታችሁንና አካባቢያችሁን በምትጠቀሙበት ጊዜ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መሆኑን የሚያሳይ ስዕል ትስላላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

4.3.1 በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች

4.3.2 በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ጥቅም

## 4.3.1. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች

### ተግባር 1.1.2 የቡድን ውይይት

ዓላማ፡- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች መዘርዘር

መመሪያ፡- በቡድን ሆናችሁ በመወያየት የተስማማችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ጥያቄ፡- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን የንድፍ ካርታ በመሳል አሳዩ፡፡



ስዕል 4.10 የትምህርት ቤት ግቢ

በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በአብዛኛው የሚገኙ ነገሮች፡-

- የስፖርት ሜዳ
- የመማሪያ ክፍሎች
- ሰንደቅ ዓላማ
- የመጸዳጃ ቤት
- ቤተ-መፅሐፍት
- የትምህርት ማበልፀጊያ ማእከልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 4.3.2. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ጥቅም

ተግባር 4.3.2 የጥንድ ዉይይት

ዓላማ፡- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን ጥቅም መዘርዘር

መመሪያ፡- ለሁለት ለሁለት በመሆን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ጥያቄ፡- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን ጥቅም አብራሩ?

በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ጥቅም

- ዛፎች ለጥላነት
- ህንፃዎች ለተለያዩ መማሪያ ክፍሎችና ቢሮዎች
- የስፖርት ሜዳ ለመጫዎቻነት
- ሽንት ቤት ለመፀዳጃነት እና ወዘተ...ናቸዉ፡፡

መልመጃ 4.3

ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. የስፖርት ሜዳ ለመጫወቻነት ያገለግላል፡፡
2. ስንደቅ ዓላማ በትምህርት ቤት ዉስጥ አይገኝም፡፡__

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚገኘዉ የቱ ነዉ?

ሀ. አባት　　ሐ. መምህር

ለ. እናት　　መ. ሁሉም

2. ቤተ-መፃህፍት ለ_______ያገለግላል?

ሀ. ለማንበብ　　ሐ. ለመሮጥ

ለ. ለመጫወት　　መ. ሁሉም

**ትዕዛዝ 3፡- በ “ሀ” ሥር ለተዘረዘሩት ተስማሚያቸውን ከ “ለ” ስር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዛፎች | ሀ. ለመጫወቻ |
| 2. ህንፃዎች | ለ. ለመፀዳጃ |
| 3. የስፖርት ሜዳ | ሐ. ለጥላ |
| 4. ሽንት ቤት | መ. ለመማሪያ ክፍሎችና ቢሮዎች |

## 4.4. በጋራ እንጫወት፤ በጋራ እንስራ



**መታወቅ የሚገባቸው ቃላት**

- ምክር
- መተሳሰብ
- መጫወት
- እኩልነት
- መረዳዳት
- ጓደኝነት

### የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በጋራ መጫወትን ትለማመዳላችሁ
- በጋራ መስራትን ትለማመዳላችሁ፡፡

## የንዑስርዕስ ይዘቶች

4.4.1 በጋራ መጫወት
4.4.2 በጋራ መሥራት

## 4.4.1. በጋራ መጫወት

### ተግባር 4.4.1 ሚና ጨዋታ

**ዓላማ:-** በጋራ መጫወትን ማሳየት

**መመሪያ:-** መምህሩ የሚሰጣችሁን ተግባር በሚና ጨዋታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

**ጥያቄ:-** ከጓደኞቻችሁ ጋር በቡድን በመሆን በአካባቢያችሁ ከሚታዉቁት ጨዋታ የተወሰኑትን አሳዩ፡፡





ስዕል 4.11 ልጆቹ ምን እያደረጉ ነዉ?

### በጋራ መጫወት:-

- መተባበርን ያጎለብታል፡፡
- መተጋገዝን ያጠነክራል፡፡
- የጓደኝነት ፍቅርን ይጨምራል፡፡
- መረዳዳትን ያጠነክራል፡፡
- መደጋገፍን ያጠነክራል፡፡


## 4.4.2. በጋራ መሥራት

### ተግባር 4.4.2 ጭውውት ወይም ክርክር

**ዓላማ፡-** በጋራ የመስራትን ጥቅም መዘርዘር

**መመሪያ፡-** በጋራ የመስራትን ጥቅም በጭውውት ወይም በክርክር መልክ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

**ጥያቄ፡-** በጋራ የመስራት ጥቅም ምንድነዉ?

ስዕል 4.12 በጋራ መሥራት

ልጆች ምን እየሰሩ ነዉ? ሰዎቹ ምን እያደረጉ ነዉ?

**በጋራ መስራት፡-**

- የሥራ ክቡርነትን ያሳያል።
- መረዳዳትን ያሳያል።
- መልካም ጉርብትናን ያጠናክራል።
- ችግሮችን ይፈታል።
- ጥሩ ውጤት ያስገኛል።

መልመጃ 4.4

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. በጋራ መጫወትና መስራት ጠቃሚ ነዉ፡፡
2. በጋራ መጫወት የጓደኝነት ፍቅርን ይጨምራል፡፡

**ትዕዛዝ 2፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. በጋራ የመስራት ጥቅም የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. መረዳዳት
   - ለ. መተጋገዝ
   - ሐ. ችግር መፍታት
   - መ. ሁሉም
2. በጋራ መጫወት ጥቅም ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. አንድነት
   - ለ. ፍቅር መጨመር
   - ሐ. መራራቅ
   - መ. ሁሉም

## 4.5. የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎች



መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ደንብ ልብስ
- ደንብ
- ንብረት
- መመሪያ

### የንዑስ ርዕስ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎች ታብራራላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎች በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

## 4.5.1. 4.5.1 የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ

### ተግባር 4.5.1 የጥንድ ዉይይት

**ዓላማ:-** ስለትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ ማብራራት

**መመሪያ:-** በጥንድ በመሆን ስለትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ጥያቄ:-** የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያዎችን ታብራራላችሁ፡፡



ስዕል 4.13 ተማሪዎች ምን እያደረጉ ነዉ?

### የትምህርት ቤት ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች

- የትምህርት መሣሪያዎችን አሟልቶ በአግባቡ መያዝ
- የትምህርት ሰዓትን ማክበር
- የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ መልበስ
- ትምህርትን በአግባቡ መከታተል
- በክፍልም ሆነ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ አለመረበሽ
- የክፍልና የቤት ሥራዎችን በወቅቱ መሥራት
- የትምህርት ቤትን ንብረት መጠበቅና መንከባከብ
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አለመጣላት፣ አለመደባደብ
- መምህራንንና የአስተዳደር ሠራተኞችን ማክበር
- ያለ ሰዓት ከትምህርት ቤት ግቢ ያለመውጣት

## መልመጃ 4.5

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ፡፡**

1. የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያን ማወቅ ተገቢ ነዉ፡፡
2. ሰዓት ማክበር የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ ነዉ፡፡___

**ትዕዛዝ 2፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡**

1. የትምህርት ቤት ደንብ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. በትምህርት ሰዓት መጫወት
   - ሐ. በሰዓቱ መገኘት
   - ለ. የደንብ ልብስ መልበስ
   - መ. ሁሉም
2. ከሚከተሉት አንዱ የትምህርት ቤት ደንብና መመሪያ **የማክበር ጥቅም ነዉ፡፡**
   - ሀ. ዉጤታማ መሆን
   - ሐ. መሸለም
   - ለ. ስነ-ምግባር ማስተካከል
   - መ. ሁሉም

## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

በአካባቢያችን የሚገኙ አስፈላጊ ዕፅዋቶች እንሰት፣ ድንች፣ ዳመከሴ፣ ባህር ዛፍ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በአካባቢያችን የሚገኙ ዕፅዋቶች በአስተዳደግ ሁኔታቸው፣ በውጫዊ ገፅታቸው እና ከሚኖሩበት ቦታ አንፃር በሶስት ይመደባሉ፡፡

በአካባቢያችን የሚገኙ እፅዋቶች ለምግብነት፣ ለመጠለያ፣ ለልብስ መስሪያና ለመድሀኒትነት ይጠቅማሉ፡፡

የቤተሰብ አባላት የምንላቸው እናት፣ አባት፣ እህቶች፣ ወንድሞች፣ አክስቶችና አጎቶች ናቸው፡፡

መተሳሰብ፣ መፈቃቀር፣ መከባበርና ታማኝነት ቤተሰባዊ መልካም ግንኙነት ናቸው፡፡

ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች ናቸው፡፡

በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎች፣ የሰንደቅ

ዓላማ፣ የመፀዳጃ ቤት፣ ቤተ-መፃሕፍት፣ የትምህርት ማበልፀጊያ ማእከል እና የመሳሰሉት ናቸው።

በትምህርት ቤት ውስጥ መልካም ግንኙነት የሚኖረው በመግባባትና በሕብረት በመስራት ነው።

የትምህርት ቤት ደንብና ሥነ-ሥርዓቶች የሚባሉት ሰዓትን አክብሮ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት፣ የደንብ ልብስ መልበስ፣ አለመረበሽ፣ ከትምህርት ቤት አለመቅረት ወዘተ… ናቸዉ።

**ትዕዛዝ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።**

1. ለልጆች በጋራ መጫወት አስፈላጊ ነው።
2. ሰንደቅ ዓላማ ትምህርት ቤት ይገኛል።
3. አባትና እናት የቤተሰብ አባላት አይደሉም።
4. ጥጥ እና ቆዳ ልብስ ለመስራት ያገለግላሉ።
5. መልካም ሥነ ምግባር ያለው ልጅ ቤተሰቡን ይረዳል።

**ትዕዛዝ 2፡- በ "ሀ" ሥር ለተዘረዘሩት ተስማሚያቸውን ከ "ለ" ስር ካሉት ጋር በመስመር አዛምዱ።**

| | ሀ | | ለ |
|---|---|---|---|
| 1 | የቤተሰብ አባል | ሀ. | ካሮት፣ ድንችና ሽንኩርት |
| 2 | ልብስ ለመስራት ያገለግላሉ | ለ. | አባት፣ እናትና እህት |
| 3 | የእናት ወንድም | ሐ. | የደንብ ልብስ መልበስ |
| 4 | ለምግብነት ያገለግላል | መ. | ጥጥ፣ ቆዳ እና ሱፍ |
| 5 | የትምህርት ቤት ደንብ | ሠ. | አጎት |

**ትዕዛዝ 3፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኘው የቱ ነው?

ሀ. ጥቁር ሰሌዳ    ሐ. መፀዳጃ ቤት

ለ. ሜዳ    መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ጥሩ ሥነ-ምግባር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. መከባበር    ሐ.መደማመጥ

ለ. ሰዓት ማክበር    መ. ሁሉም

3. መጠለያ ለመስራት የሚያገለግለው ዕፅዋት የቱ ነው?

ሀ. እንጨት    ሐ. ባህር ዛፍ

ለ. ሳር    መ. ሁሉም

4. ጥሩ ጎረቤት የሚባለው _____ ነው

ሀ. የሚረዳዳ    ሐ. ችግር የሚካፈል

ለ. ደስታ የሚካፈል    መ. ሁሉም

5. ለአንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ምግብ    ሐ. መንገድ

ለ. መጠለያ    መ. ሁሉም

# ምዕራፍ አምስት

# የተለየ ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ ጉዳዮች

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የትራፊክ ደንቦችን ትገልፃላችሁ::
- የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት በተግባር ታሳያላችሁ::
- የመኪና መንገድ ላይ አደጋዎችን ትገልፃላችሁ::
- የመኪና መንገድ ወይም የትራፊክ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ታብራራላችሁ::
- ስለት ያላቸዉን ነገሮች ያለመጠቀም ልምድን ታዳብራላችሁ::
- ራሳችሁን ለአደጋ ከመጋለጥ የመጠበቅ ጥንቃቄ ልምድ ትተገብራላችሁ::
- ከቆሻሻዎች ጋር ያለዉን ንኪክ የማስወገድ ዘዴዎችን ትገልፃላችሁ::

## መግቢያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ልዩ ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ ጉዳዮች በተለይም የትራፊክ ደንቦችን እና በመንገድ ላይ ስለሚወሰዱ ጥንቃቄዎች፣ ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ በተመለከተ የምትማሩ ይሆናል፡፡

### በምዕራፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች

5.1 የመንገድ አጠቃቀም

5.2 ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ

## 5.1. የመንገድ አጠቃቀም



### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ግራ
- ቀኝ
- የመንገድ አጠቃቀም
- እግረኛ ማቋረጫ/ ዜብራ
- የትራፊክ መብራት

### ከንዑስ ርዕስ የሚጠበቁ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-

- የመንገድ አጠቃቀም ስርዓት በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- የመኪና መንገድ ላይ አደጋዎችን ትገልፃላችሁ፡፡
- የመኪና መንገድ ወይም የትራፊክ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ታብራራላችሁ፡፡

### በንዑስ ርዕስ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች

5.1.1 የመንገድ አጠቃቀም

5.1.2 የመንገድ ላይ አደጋዎች

5.1.3 የመንገድ ላይ አደጋዎችን መከላከል

## 5.1.1.5.1.1 የመንገድ አጠቃቀም

### ተግባር 5.1.1 የጥንድ ውይይት

**ዓላማ:-** ስለ መንገድ ላይ ደህንነት መግለፅ

**መመሪያ:-** ተማሪዎች! ስለ መንገድ አጠቃቀም በጥንድ በመወያየት የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ:-** ስለ መንገድ አጠቃቀም በዝርዝር አብራሩ።

ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱም ሆነ ስትመለሱ ማድረግ የሚገባችሁ ጥንቃቄዎች:-

- በመንገዱ በግራ በኩል ብቻ መጓዝ
- ለሰው በተፈቀደው እግረኛ ማቋረጫ/ ዜብራ ምልክት ማቋረጥ
- በመኪና መንገድ ላይ አለመጫወት
- የትራፊክ መብራት በአግባቡ መጠቀም




ስዕል 5.1. ሀ. የግራ መንገድ አጠቃቀም

ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን ለመምራችሁ ተናገሩ።





ስዕል 5.1. ለ. የእግረኛ ማቋረጫ ወይም ዜብራ አጠቃቀም

ለሰው በተፈቀደው የእግረኛ ማቋረጫ ወይም ዜብራ ምልክት ማቋረጥ ያስፈልጋል።




ስዕል 5.1. ሐ. የትራፊክ መብራት አጠቃቀም

**በስዕሉ ላይ የምትመለከቱት ምንድነው? አገልግሎቱስ?**

## 5.1.2. የመንገድ ላይ አደጋዎች

### ተግባር 5.1.2 የማስተዋል ጥያቄ

**ዓላማ:-** የመንገድ ላይ አደጋዎችን መናገር

**መመሪያ:-** ተማሪዎች! ስለ የመንገድ ላይ አደጋዎችን በጥንድ በመወያየት የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ:-** የመንገድ ላይ አደጋዎች ምንድን ናቸው?



የመኪና ግጭት



በመኪና መገልበጥ ሰዎች ሲጎዱ



የመኪና መገልበጥ

ስዕል 5.2 የመንገድ ላይ አደጋዎች

የመንገድ ላይ አደጋዎች የሚባሉት:-

የመኪና ግጭት፣ የመኪና መገልበጥ፣ የሰዎች ሞት እና የመሳሰሉት ናቸዉ::

## 5.1.3. የመንገድ ላይ አደጋዎችን መከላከል

### ተግባር 5.1.3 የጥንድ ውይይት

ዓላማ:- የመንገድ ላይ አደጋዎችን መከላከል

መመሪያ:- በጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ውጤቱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

ጥያቄ:- የመንገድ ላይ አደጋዎችን እንዴት እንከላከል?

የመንገድ ላይ አደጋዎችን ለመቀነስ:-

- በመኪና መንገድ ላይ ንቃት ባለው ሁኔታ መጓዝ
- ቀኝና ግራን ተመልክቶ መንገድ ማቋረጥ
- በእግረኛ ማቋረጫ ወይም ዜብራ ምልክት ማቋረጥ
- ድልድዮችን፣ መረማመጃዎችንና የሚያዳልጡ ቦታዎችን በጥንቃቄ ማለፍ
- በመንገድ ላይና በመንገድ ዳር አለመጫወት
- የመንገድ ላይ ማቋረጫ መስመሮችን በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም

የመኪና መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ሌሎችን ማለትም:-

- ሕፃናትን መርዳት
- አዛውንቶችን መርዳት
- አካል ጉዳተኞችን መርዳት ያስፈልጋል

## መልመጃ 5.1

**ትዕዛዝ 1:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ::**

1. የመንገድ ላይ አደጋ የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. የመኪና ግጭት
   - ለ. የመኪና መገልበጥ
   - ሐ. የሰው መገጨት
   - መ. ሁሉም
2. የመንገድ ላይ አደጋዎችን እንዴት መከላከል ይቻላል?
   - ሀ. የመንገዱን ግራ ይዞ መጓዝ
   - ለ. በዜብራ ማቋረጥ
   - ሐ. መንገድ ላይ አለመጫወት
   - መ. ሁሉም

**ትዕዛዝ 2:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ::**

1. የመንገድ ላይ አደጋዎችን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት?
2. የትራፊክ መብራት ቀለሞችና አገልግሎታቸውን ተናገሩ::

## 5.2. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ



### መታወቅ የሚገባቸው ቃላት

- ልማድ
- ጤና አጠባበቅ
- ስለታም ነገሮች
- አክታ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ትገልፃላችሁ::
- ስለት ያላቸዉን ነገሮች ትዘረዝራላችሁ::
- ስለት ያላቸዉን ነገሮች ያለመጠቀም ልምድን ታዳብራላችሁ::
- ከቆሻሻዎች ጋር ግንኙነት/ንኪክ ማስወገድ ወይም ራሳችሁን ለአደጋ ከመጋለጥ የመጠበቅ ጥንቃቄ ልምድ ትተገብራላችሁ::

## በንዑስ ርዕስ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች

5.2.1 ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ምንድን ነዉ?
5.2.2 ስለታም ነገሮችን ያለመጠቀም
5.2.3 ከቆሻሻዎች ጋር ግንኙነት/ንኪክ ያስወግዱ

## 5.2.1. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ምንድነዉ?

### ተግባር 5.2.1 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** ስለ ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ መናገር

**ጥያቄ፡-**
1. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ምንድነዉ?
2. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ያለመከተል ምን ችግር ያስከትላል?

ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ማለት ግለሰቦች ጤንነታቸውን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል እና የጤና ችግሮችን ለመቀነስ የሚወስዱት እርምጃ ነዉ::

ሁላችንም የተለያየ በሽታ የመከላከል አቅም አለን::

ሰዎች ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ እንዲያዳብሩ ማበረታታት ደህንነትን ለማስጠበቅና የሕክምና ወጪን በእጅጉ ለመቀነስ ይረዳል::

ዋና ዋና የጤና ጠባዮች ወይም መደቦች የሚባሉት በሽታ እና በሽታ መከላከል ናቸው::

በሽታ የመከላከል ልማድ ማለት በሽታን ለመከላከል የሚወሰድ ማንኛውም ተግባር ማለት ነዉ::

በሽታ መከላከል ማለት በበሽታዉ ሳይያዙ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ነዉ::

## 5.2.2. ስለታም ነገሮችን ያለመጠቀም

### ተግባር 5.2.2 የቡድን ውይይት

**ዓላማ፡-** ስለታም ነገሮች ያለመጠቀምን መለማመድ

**መመሪያ፡-** ስለ ስለታም ነገሮች አጠቃቀም በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ጥያቄ፡-** 1. ስለታም ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡

2. ስለታም ነገሮችን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንችላለን?

ዉድ ልጆች! ስለታም ነገሮችን እንዴት ትጠቀማላችሁ?

ስለታም ነገሮች የሚባሉት፡- ምላጭ፣ መርፌ፣ ቢላዋ፣ ጥፍር መቁረጫ፣ መቀስ የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

እነዚህን ስለታም ነገሮች በተገቢዉ መንገድ መጠቀም ይኖርብናል፡፡


ምላጭ፣ መርፌና ጥፍር መቁረጫ ሁሉም ሰዉ በየግል መጠቀም ያለባቸዉ ዕቃዎች ናቸዉ፡፡

እነዚህን ስለታም ነገሮች በጋራ የምንጠቀም ከሆነ ለተለያዩ በሽታዎች (ለምሳሌ ለኤች አይ ቪ ኤድስ) ልንጋለጥ እንችላለን፡፡



ስዕል 5.3. ሀ. በጋራ መጠቀም የማይገቡ ቁሳቁሶች

ስለታም መሳሪያዎች በተገቢው መንገድ ካልተያዙ መቆራረጥ እና መቁሰል ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡



ስዕል 5.3. ለ. በጋራ መጠቀም የማይገቡ ቁሳቁሶች

### 5.2.3. ከቆሻሻዎች ጋር ያለዉን ንኪክ ማስወገድ

**ተግባር 5.2.3 የቡድን ውይይት**

**ዓላማ:-** የተለያዩ ቆሻሻዎች ንኪክ ማስወገድን መግለፅ

**መመሪያ:-** የተለያዩ ቆሻሻዎች ንኪክ ማስወገድን በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ጥያቄ:-** የቆሻሻዎች ንኪክን ለማሰወገድ ምን መደረግ እንዳለበት ተናገሩ።

የተለያዩ በደምና በአክታ የተነካኩ ወረቀቶችንና ዕቃዎችን ባለመንካትና ባለመጠቀም ራሳችንን ከቆሻሻ ንኪክ መጠበቅ ይኖርብናል።

የቆሻሻ ንኪክዎችን ለማስወገድ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርብናል።

- አካባቢን ማፅዳት
- በየቦታዉ የተጣሉ ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ማቃጠልና በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዉስጥ መጣል
- በደምና በአክታ የተነካኩ ወረቀቶችን ወይም ሶፍቶችን ያለመንካትና በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዉስጥ መጣል
- ሌላ ሰው የተጠቀመበትን የጥርስ ብሩሽ አለመጠቀምና ያለመንካት

## መልመጃ 5.2

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።**

1. ማንኛዉንም ቆሻሻ መነካካት ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል።
2. ስለታም ነገሮችን በጋራ መጠቀም ለአደጋ ያጋልጣል።
3. መርፌና ምላጭ ስለታም የሆኑ ቁሳቁሶች ናቸዉ።

## ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ከሚከተሉት አንዱ ለተለያዩ በሽታዎች ሊያጋልጠን **ይችላል**።
   - ሀ. ቆሻሻ ላይ መጫወት
   - ለ. የግል ንፅህናን መጠበቅ
   - ሐ. ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ማቃጠል
   - መ. ሁሉም
2. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ማቃጠል
   - ለ.ቆሻሻዎችን ጉድጓድ ዉስጥ መጣል
   - ሐ.የግልና የአካባቢ ጤና መጠበቅ
   - መ. ሁሉም
3. ከሚከተሉት ስለታም ነገሮች አንዱ ሰዉነትን ይጎዳል።
   - ሀ. ምላጭ
   - ለ. መቀስ
   - ሐ. ቢላዋ
   - መ. ሁሉም

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

የመንገድ ደህንነት ህግና ደንቦች በጣም አስፈላጊ ናቸው። ምክንያቱም ህግና ደንቦችን ማክበር ራሳችንን ከመንገድ አደጋዎች እንድንጠብቅ ይረዳናል።

ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ግለሰቦች ጤንነታቸውን ለመጠበቅ ወይም ለማሻሻል እና የጤና ችግሮችን ለመቀነስ የሚወስዱት እርምጃ ነዉ።

ሰዎች ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ እንዲያዳብሩ ማበረታታት ደህንነትን ለማስጠበቅና የሕክምና ወጪን በእጅጉ ሊቀንስ ይችላል።

ስለታም ነገሮች የሚባሉት:- ምላጭ፣ መርፌ፣ ቢላዋ፣ ጥፍር መቁረጫ፣ መቀስ የመሳሰሉት ናቸዉ።

እነዚህን ስለታም ነገሮች በተገቢዉ መንገድ መጠቀም ይኖርብናል።

የተለያዩ በደምና በአክታ የተነካኩ ወረቀቶችንና ዕቃዎችን ባለመንካትና ባለመጠቀም ራሳችንን ከቆሻሻ ንኪክ መጠበቅ ይኖርብናል።

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ትዕዛዝ 1:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።**

4. የትራፊክ ህግን ያለማክበር ለአደጋ ያጋልጣል።
5. መንገድ ስናቋርጥ የእግረኛ ማቋረጫ ወይም ዜብራን መጠቀም አለብን።
6. የመንገድ ደህንነት ህግና ደንቦችን ማክበር አስፈላጊ ነው።
7. ስለታም የሆኑ ዕቃዎችን በጋራ ብንጠቀም የጤና ጉዳት አያስከትልም።

**ትዕዛዝ 2:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ።**

1. ከሚከተሉት አንዱ የትራፊክ አደጋን ያስከትላል
   - ሀ. መንገድ ላይ መጫወት
   - ሐ. ቀኝ መንገድ መጠቀም
   - ለ. የእግረኛ ማቋረጫን መጠቀም
   - መ. ሀ እና ሐ
2. ከሚከተሉት የትኛው ለበሽታ ሊያጋልጠን ይችላል?
   - ሀ. ስለታም ዕቃዎችን በጋራ መጠቀም
   - ለ. ንፅህና መጠበቅ
   - ሐ. ቆሻሻ ያለመንካት
   - መ. ሁሉም
3. የቆሻሻ ንኪክዎችን ለማስወገድ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
   - ሀ. ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ማቃጠል
   - ለ. ቆሻሻዎችን ጉድጓድ ዉስጥ መጨመር
   - ሐ. በቆሻሻ ቦታዎች ላይ አለመጫወት
   - መ. ሁሉም
4. ከሚከተሉት ዉስጥ ስለታም ነገር ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ.መርፌ
   - ለ. ምላጭ
   - ሐ. ጫማ
   - መ. ሁሉም
5. ሰዎች ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልምድ ሲኖራቸዉ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
   - ሀ. የህክምና ወጪያቸዉን ይቀንሳል
   - ለ. ሙሉ ጤነኛ ይሆናሉ
   - ሐ. ለተለያዩ በሽታዎች አይጋለጡም
   - መ. ሁሉም

# ዋቢ መጽሐፍት


1. በትምህርት ሚንስቴር የተዘጋጀ የአዲሱ ፍኖተ-ካርታ አጠቃላይ ስርዓተ-ትምህርት መጋቢት 2013 ዓ.ም
2. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ትም/ት ቢሮ የተዘጋጀ የ1ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ (2004 ዓ.ም)
3. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ትም/ት ቢሮ የተዘጋጀ የ2ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ (2004 ዓ.ም)